# ምዕራፍ 3

## የሥራ ዓለም

### በጅማ በር ራዲዮ ጣቢያ

የመጀመሪያው አመት የትምህርት ትኩረት ኤሌክትሪክ ላይ ስለነበር ስለ ኤሌክትሪክ ንድፈ ሃሳቡን ከማወቅ አልፈ አንድ የኤሌክትሪክ ባለሙያ ሊሠራ የሚገባውን ማወቅ ቻልኩ። በዚህ ጊዜ ከደደር ከወጣሁ አመትም አልሞላኝም ነበር:: በሁለተኛው አመት ደግሞ ስለ ራዲዮ ተማርን፤ በራዲዮ ውስጥ ያሉት ነገሮች ሁሉ ተሰጥተውን ራዲዮ ሠርተናል:: እኔ የሠራሁዋት ራዲዮ የአንድ አገር ጣቢያ በማግኘት ከከፍሌ የመጀመሪያዋ ነበረች። በዚህ ውጤቴ የራዲዮ ክፍል ረዳት አስተማሪዬ ጋሼ አሸቴ በጣም ተደስቶ ነበር።

የሁለተኛው ዓመት የራዲዮ ትምህርታችን ስለ መሳቢያው (Receiver) ሲሆን በሶስተኛ አመት መጀመሪያ ተርም ይህን አጠናቀን ወደ መላኪያው (Transmiter) መሸጋገር ነበረብን። በመጀመሪያው ተርም መጨረሻ የቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤት ወደ ትምህርት ቤታችን መጥቶ እስከ ሰኔ ወር አልጠብቅም፣ የራዲዮ ሾፕ ተማሪዎች የሆኑት አሰራ አንድ ወጣቶች እንደ ራዲዮ ቴክኒሺያን አቀጥራችዋለሁ አለ:: እኛም ተስማማን ስለዚህ ከጥር 1 ቀን 1947 ዓ ም ጀምሮ የቴሌ ተቀጣሪ ሆኜ በጅማ በር (አየር ጤና) የመላኪያ ራዲዮ ጣቢያ ስራዬን ጀመርኩ።

***

ጥር ወር መጨረሻ በህይወቴ ልዩ ስሜት የተሰማኝ ቀን ነበር:: ከዚያን ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ተሰምቶኝ የማያውቅ ድንቅ የሆነ የከበርቴነት ስሜት የተሰማኝ





ቀን:: ደሞዜ በፖስታ ዉስጥ ተደርጎ ተሰጠኝ:: ቆጠርኩት፤ 147.50 ብር በጣም ብዙ ነበር::

ወዲያውኑ ፒያሳ ሄጄ ዳርማር ከሚባል የጫማ ሱቅ በ18.00 ብር ሲረግጡበት ድምጼ የማይሰማ ጫማ ገዛሁ:: ሶሉ ቆዳ፣ ተረከዙ ላይ ብረት የተሰጠፈበትንና ሲራመዱበት ድምፅ የሚያወጣውን የቀድሞ ጫማዬን ወዲያ ጣልኩ:: በተጨማሪ አንድ ሳፈያን ኮትና ሱሪ ገዛሁ:: ዘነጥኩ ማለት አይደል? በመቀጠል እስ አይ ኤም መጻሕፍት መደብር ሄጄ አንድ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስና GEM DICTIONARY ገዛሁ። ከዚያም ወደ ድሬዳዋ ለወንድሜ ለአሸብር 10 ብር በፖስታ አርጌ በሬኮማንዴ ላኩለት:: አሸብር ያኔ ዘመድ ዘንድ ተጠግቶ ድሬዳዋ ክርስቶስ ትምህርት ቤት ይማር ነበር::

ደብዳቤው ሲሰጠው ሰመከፈት ተርበተበተ፤ ሰምን በሬኮማንዴ ተላከ? እስ፤ ፖስታውን በአግባቡ በመከፈት ፈንታ በአንድ በኩል በጥርሱ ቅርጥፍ አድርጎ ከፈተው:: ፖስታው ውስጥ ከአንድ በኩል ጫፏ ቅርጥፍ የተደረገች አስር ብር አየ፤ በጣሙን ተደሰተ:: ይህን የሚያህል ብር ኪሱ ገብቶ አያውቅም ነበርና::

***

### እምነቴና ሃይማኖቴ

ቴሌ ሥራ ስንጀምር ከጓደኛዬ ጸጋ ጋር ተሰያየን:: እኔ ጂማ በር ራድዮ ጣቢያ (transmitting station) ስመደብ እርሱ አቃቂ ራዲዮ መቀበያ ጣቢያ (receiving station) ነበር የተመደበው:: ሥራችን ትራንስሚተሩን አዘጋጅቶ ለአዲስ አበባ ራዲዮ ወይም ለፍል ውኃ ቴሌፎን ጣቢያ መስጠት ነበር። ቀላል ቢሆንም ቁጭ ብለን መጠበቅ ነበረብን:: ሥራው ሳያቋርጥ ለ24 ሰአት የሚከናውን ነበር፤ በየፈረቃችን 8 ሰአት ሰርተን እንወጣና ከ24 ሰአት በኋላ ተመልሰን እንገባለን።

የሥራ ባልደረቦች እፎይታ ሲያገኙ መጨዋወታቸው አይቀርምና በጊዜው እኔ በአብዛኛው ማወራት የምወደው መጽሐፍ ቅዱስ ነክ ነገሮችን ነበር። አንድ ቀን

በጣም ከምወደውና ከማከብረው ጋሼ መርሻ ጋር ተረኞች ሆነን ስንሠራ ወደ ማታ ላይ እንደ ልማዳችን ስንጨዋወት እንዲህ በማለት ጠየቀኝ፡- "አንተ ሚሊዮን ሃይማኖትህ ምንድነው? ኦርቶዶክስም አይደለህም፤ ደግሞም ከባልደረቦችን ሌዊ ጋር ስለ ማትስማማ ካቶሊክ እንዳልሆንክ አውቃለሁ፤ ፕሮቴስታንት ነህን?" በማለት ጠየቀኝ፡፡ እጠያየቁ አስደነገጠኝ፡፡ "አይ አኔ ፕሮቴስታንት አይደለሁም" እልኩት። ምክንያቱም እስከዚያች ቀንና ሰዓት ድረስ እራሴን እንደ ጥሩ ኦርቶዶክስ እቆጥር ስለ ነበር በጥያቄው ደነገጥኩ፡፡ "ታዲያ ምንድነህ?" አለኝ።

"እኔ መቼም መጽሐፍ ቅዱስን እነባለሁ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ሳነበው ኃጢአተኛ ነህ ብሎኛል፤ እንደ ሆንኩም አወቅኩ፡፡ በኃጢአቴ ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቼአለሁ፤ እንዲሁ ብቅጥል የምሄደው ወደ ገሐነመ እሳት እንደምሄድ ተረዳኹ፡፡ ግን እግዚአብሔር ወደ እዚያ እንድሄድ ስለማይፈልግ በእኔ ምትክ እንዲሞት አንድያ ልጁን ልኮልኛል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኔ በመስቀል ላይ እንደ ሞተልኝ ተረድቻለሁ፡፡ ከአሁንም ወዲያ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበብሁ እርሱን መከተል ነው ምርጫዬ" አልኩት። በአስተያየቴ ሲስማማ ደስ አለኝ፡፡

ያን ለት ማታ ከሥራ ስመለስ ከጋሼ መርሻ ጋር ስለ ተነጋገርነው ነገር በጥልቀት አሰብሁ፡፡ በተለይ ኦርቶዶክስ አይደለህም ማለቱ አሳሰበኝ፡፡ ታዲያ "እኔ የማንን አስተምህሮ ነው የምከተለው ብዬ ራሴን ጠየቅሁ"፡፡ ሦስት አስተማሪዎቼ ፊቴ ድቅን አሉ፡፡

አንደኛው መምሬ በቀለ የእናቴ ነፍስ አባት (የእኔም ነፍስ አባት) እና የልደታው ካኅን ትምህርትም በጥቂቱ አሉበትና ሁለቱን እንደ አንድ እቆጥራቸዋለሁ፡፡ ሁለተኛው ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ምሩቅ የሆነው የሞራል መምህሬ፤ ሲሆን እርሱም እንደ እኔ የኦርቶዶክስ አስተምህሮችንና ሥርዓተ አምልኮችን ሙሉ በሙሉ ለመቀበል የሚያዳግተው ሰው ነበር፡፡ ሦስተኛዎቹ ሚስዮን ቤት ስሄድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምሩኝ ሰዎች ናቸው፡፡

ከሁሉም የቀሰምኳቸውን ትምህርቶች ለማሰብ ሞከርኩ፡፡ እራሴን ጠየቅኩ። "እነኚህ ሁሉ ሰዎች የሚያስተምሩትን ከየት አመጡት? ከመጽሐፍ ቅዱስ አይደለምን? ታዲያ እነርሱ ስለ ክርስትና መሠረታዊ ነገሮች ባስተማሩ ቁጥር የሚጠቅሱት መጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ እኔስ መጽሐፍ ቅዱስን እየመረመርኩ እውነቱን መረዳት አልችልምን?" አልኩ። ለጋሼ መርሻ እንዳልኩት ማንም፣ ምንም ይበለኝ ምን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እከተላለሁ አልኩ።





ይህን ውሳኔዬ ከሁለት ሳምንት በፊት እሁድ ጠዋት ልደታ ቤተ ክርስቲያን ከቅዳሴ በኋላ የተከሰተውን ነገር መለስ ብዬ እንዳስታውስ አደረገኝ፡፡ እኔና ጸጋ ከቅዳሴ በኋላ እንደ ልማዳችን አንድ ማማ ላይ ወጥተው ተዓምረ ማርያምን የሚያስተምሩትን ካኅን እናዳምጣለን፡፡ እኚህ ቄስ ሁል ጊዜ የሚያስተምሩት አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ስለ ተአምረ ማርያም። የዚያን እሁድ ጠዋት ግን ቅዳሴው እንዳለቀ አንድ ባህታዊ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው፡-

"ንስሃ ግቡ፤ እናንተ ሳምንቱን ሁሉ ስታታልሉ ስንብታችሁ አንድ ሁለት ብር መንዝራችሁ መጥታችሁ የምትበትኑ፣ ንስሃ ግቡ፤ ከፉ ሥራ መሥራት አቁሙ . . . " እያሉ መስበክ ጀመሩ፤

ስብከታቸው የመጥምቁ ዮሐንስ አይነት መሰለኝ፡፡ ሕዝቡ ግልብጥ ብሎ ወደ እሳቸው ሄደ፤ እኛም ተከትለን ሄደን መስማት ጀመርን፡፡

ማማው ላይ ሆነው ያስተምሩ የነበሩት ቄስ በቁጣ መቆሚያቸውን እየወዘወዙ መጡና "ማን አስተማሪ አደረገህ?" ብለው ባህታዊውን አባረሩዋቸው። ባህታዊው ብቻቸውን አልነበረም የወጡት። ብዙ ሰው፣ እኛንም ጨምሮ ግቢውን ለቀን ወጣን። ከዚያ ቀን በኋላ ልደታ ቤተ ክርስቲያን መሄዴን አቆምኩ።

ይህን ከስተት ደግሜ ማስታወሴ ሰባኪዎች የሚሉትን ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን በግል እንብቦ መረዳት ዋጋ አለው የሚለውን አቋሜን እንዳጸና አደረገኝ። ከዓመታት በኋላ የኢትዮጵያም የአፍሪቃም መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ዋና ጸሐፊ እንድሆን ያደረገኝ ይህ አጀማመሬ እንደ ሆነ እገምታለሁ፡፡ ኋላ ላይ ሰዎች በሚገባቸው ቋንቋና ሊገዙ በሚችሉት ዋጋ መጽሐፍ ቅዱስን ለሕዝቤና ለመላው

አፍሪቃውያንም ማቅረብ ዋና ሥራዬ ሆኖ እንዴት እንደ ዘለቀ በቦታው በሰፊው አተርከላችኋሁ።

***

## ዕድል ፈንታና የልብ ማመንታት

ሰኔ ወር መጨረሻ የተግባረዕድ ተማሪዎች ከልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ-ወሰን የምስክር ወረቀታችንን ተቀብለን ተመረቅን። ከላይ እንደ ገለጽኩት የራዲዮ ሾፕ ተማሪዎች ቀደም ሲል ቴሌ ሥራ ጀምረናል:: ሌሎች ጓደኞቻችን ሥራ መፈለግ ጀመሩ። በወቅቱ የባሕር ኃይል ትምህርት ቤት እንደ አዲስ ተከፍቶ ምዝገባው በተግባረ ዕድ ዲሬክተር አማካኝነት እየተካሄደ ነበር:: የመጀመሪያዎቹ 16 የባሕር ሐይል ተመዝጋቢዎች ከኔ ጋር አብረው የተመረቁ ጓደኞች ነበሩ:: ይህ ተቋም ስኮላርሺፕም ይሰጣል ስለተባለ እኔም ቴሌን ትቼ እዚያ ለመግባት ፈለግሁ::

ልመዘገብ ወደ ዲሬክተርሩ ሄድሁ፤ የሌሎቹን ስም መዘገበ፤ ተራዬ ደርሶ ስሜን ለነግረው መመዝገቡን ትቶ ቀና ብሎ አየኝ:: አለተያየቱ ደስ አላለኝም፣ እንዲያውም አስደነገጠኝ:: ለምን ይገረምመኛል ብዬ አሰብኩ:: "ሚሊዮን በለጠ፣ አንተን ሚስተር ሜታ (የራዲዮ አስተማሪዬ) ረዳቱ እንድትሆን መርጦሃል፤ ስለዚህ በአለተማሪነት ልንቀጥርህ ወስነናል፤ የአስኮላርሺፕ እድልም አለ፤ ይህን ብትተወው ይሻልሃል" ሲል መከረኝ:: በተማርኩበት ት/ቤት መምህር ሆኜ ለመቀጠር በመመረጤና የስኮላርሽፕ ዕድል እንደማተኝ ማወቁ ታላቅ ደለታን ፈጠረልኝ:: ባሕር ኃይል መግባቱን ተውኩት:: ይህ የተከሰተው በ1947 ዓ.ም. መጨረሻ ነበር

(ከብዙ አመታት በኋላ በ1961 ዓ.ም. ለመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ሥራ ወደ አስመራ ሄጄ ነበር፤ በአግረ መንገዴም ባሕር ኃይሉን እንድጎበኝ ወደ ምፅዋ ሄድሁ፤ ምጽዋ ከደረስሁ በኋላ ባህር ኃይሉን ለመጎብኘት ወደ ቢዙ ሄድሁ፤ እዛ እንደደረስሁ ፈቃድ ጠይቄ ቢዙ ገባሁ። ወዲያው ወደ መዝናኛ አዳራሻቸው ተወሰድሁ። ጓደኞቼ ሁሉም ኮመዶሮች ሆነዋል፤ ውብ የሆነውን የማዕረግ ልብሳቸውን እያመስከትኳቸው:- ባሕር ኃይል አብሬአቸው ለመግባት የነበረኝን ፍላጎት እያስታወስኩ። "ለመሆኑ ይች ነገር አመለጠችኝ? ወይስ አመለጥኳት?" ስል ጠየቅኋቸው፤ ከኮሞዶር እስከንድር በታች የቢዙ አዝዥ የነበረው ኮመዶር በለገ በለጠ " አመልጥካት እንጂ ያመለጠህ ነገር የለም" ሲለኝ ምርጫዬን ያጠናልኝን እግዚአብሔርን አመስገንኩ።)

***

ወደ ኋላ ልመልሳችህና ጂማ ራዲዮ ጣቢያ የሠራሁት እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1947 ዓ.ም ሲሆን ደሞዜም በወር 150.00 ብር ነበር:: ከመስከረም 1 ቀን 1948 ዓ ም ጀምሮ በተግባረ ዕድ ት/ቤት በመምህርነት ለመደብ ደሞዜ ወደ 200.00 ብር አደገ፤ መኖሪያዬን በመርሐ አውራን ት/ቤት ግቢ አደረግሁ። ከእኔ ሌላ:- በየነ ጭምጫ አይበሱ፣ ኃይሌ ወልደ ሚካኤል፣ እንግዳ አለፋው፣ ደለታ ዓለሙ በዚያው የመርሐ አውራን ት/ቤት ግቢ ውስጥ ነበር የምንኖረው። ለተማሪዎቹ የሚከፈለውን እየከፈልን፣ ተማሪዎቹ የሚበሉትን እየተመገብን ነበር የምንኖረው። በዚያ መኖሬ በክርስትና ሕይወቴ እንዳድግ በጣም ረዳኝ።

በዚያን ዘመን ከክርስትና መሠረታዊ ጉዳዮች ያስቸገረኝ አንዱ የጥምቀት ነገር ነበር፤ በ40 ቀኔ እንደተ ጠመቅሁ፣ የክርስትና ስሜም እምደ ማርያም እንደሆነ ተነግሮኛል:: ስለዚህ ጥምቀት አያስፈልገኝም ብዬ አምን ነበር። ይህን የጎልማላ ጥምቀት ያስተማረው የመጀመሪያው እና ባፕቲስት ቀድሞ የካቶሊክ ቄስ የነበረው ሜኖ ሳይመንስ መሆኑን በቆይታ ተረዳሁ። ሜኖ ሳይመንስ እንዲህ ብሎ በማስተማሩ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ላይሆን በሉተራውያንም ዘንድ ተወግዞአል። ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የሜኖናይት ሚስዮኖችም የሚያስተምሩት ይህን የሜኖ ሳይመንስ አለተምህሮ ነበር። እኔም ራሴ የሕፃን ጥምቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልጌ ላገኝ አልቻልኩም፤ ስለዚህም በቃሉ ተሸንፍኩ።

በመጨረሻም በየነ ጭጫ አይበሉ አኔንና፣ ሲስተር አበባ ወልደ ሩፋኤልን ለአዋቂ ጥምቀት አዘጋጅቶን በአስፋው ባቾሬ እጅ ነሐሴ 6 ቀን 1947 ዓ.ም ተጠመቅን። የአዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አጥቢያ የመጀመሪያዎቹ ተጠማቂዎች ነበርን ማለት ነው።

## ስለ ሕይወት ጓደኛ የመጀመሪያ ግንዛቤዬ

እኔና አበባ የጀመርነው ሥልጠና እርብ ሊጠናቀቅ ሐሙስ በምሣ ሰዓት ላይ ሸሚዝ ለማጠብ በየነንና አበባን ጥያቸው ሄድኩ። አጥቤ ስመለስ ከቀድሞው በተለየ አቀማመጥ ተቀራርበው አየኋቸው። ግራ ገባኝ። ወንዶች እንደዚያ ተጠጋግተን እንቀመጣለን እንጂ ከሴት ጓደኞቻችን ጋር እንደዚህ ተቀራርበን ተቀምጠን አናውቅም። ነገሩ ግር ቢለኝም "እኛ ወንድማማቾችና እህትማማቾች ነን፤ ምን አለበት" ብዬ ተውኩት። በማግሥቱ እንደዛው ተጠጋግተው እጅ ለእጅ ተያይዘው ተቀምጠው ትምህርቱን ቀጠልን። ትምህርቱን ልናቆም ስንል፡ በየነ እንዲህ አለኝ። "ከትላንትና ጀምሮ በእኔና በአበባ ሁኔታ ባየኸው ሳትገርም አልቀረህም። እኔና አበባ ሕይወታችንን ተሰጣጥተናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ብቻውን ሊሆን አይገባም ረዳት ያስፈልገዋል ስለሚል አበባ የእኔ ረዳት ለመሆን ፈቃደኛ ሆናለች፤ እንግዲህ አንተም እንዲሁ ረዳት ያስፈልግሃል" አለ። ደነገጥሁ፤ ምን እንደሚባል፤ አላወኩም ስፈራ ስቸር "ጥሩ ነው፤ ደስ ይለኛል" አልኩ። በልቤ ግን "ይሄም አለ እንዴ?" አልኩ።

ስለ ጉዳዩ አጥብቄ ማሰብ ጀመርኩ፤ ከምናውቃቸው ልጃገረዶች የትኛዋ ነች የኔ? የትኛዋን ልጠይቅ? የሚል ምርጫ ውስጥ ገባሁ። ከኃይሌና እንግዳ ጋር ውይይት ጀመርን፤ ያሉትን ልጃገረዶች በሃሳብና በደመ ነፍስ ደረጃ ተከፋፈልናቸው፤ ገፋንበትም። እንግዳ በነገሩ ቢስማማም ሊገፋበት አልፈለገም፤ እኔና ሃይሌ በልባችን ለተከፋፈልናቸው ልጃገረዶች ጥያቄ እንኳን ለማቅረብ ድፍረት አጣን፤ ነገር ግን በህልምም በእውንም እየተመላለሱብን ተቸገርን።





የበየነና የአበባ መታጫጨት ይፋ ሆነ። ከኛ ራቅ ብሎ የሚገኘው ንጉሤ አየለም ሲስተር ምህረትን መርጦ በኩርኩር (በአሁን ጊዜ በጃጅ የምትመስል) ሽርሽር መውጣት ጀምረዋል። እኔና ኃይሌ በሃሳብ ደረጃ የያዝናቸው ልጃገረዶች በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል ነርሶች ነበሩ። እኔና ኃይሌ ጥያቄአችንን ለማሳወቅ ደብዳቤ ልንጽፍላቸው ተመካከርን፤ ጽፈንም አበባ እንድታደርስልን ሰጠናት። የደብዳቤውን መልስ በጉጉት ስንጠብቅ ወስዳ ስትሰጣቸው የጭቃ ጅራፍ እንዳወረዱባት ነገረችን።

ምላሻቸው ግራ አጋባን "እኛ እንደ ተሰማን እንዴት አልተሰማቸውም? ለእኛ ያሳሰበን መንፈስ ለእነርሱስ አልተናገረም እንዴ?" በማለት በጣም ተረበሽን። ጭራሽ ለጥቂት ጊዜ ሁለቱም ልጃገረዶች ለጸሎት ሳይመጡ ቀሩ። አበባ ታላቃቸው እንደ መሆንዋ መጠን መከረቻቸው መሰለኝ ከቀናት በኋላ ጸሎት መካፈላቸውን ቀጠሉ።

ኃይሌ የመረጣት ልጅ ዓይንህን ላፈር አለችው። ዋና ምክንያትዋ እርሷ አማራ እርሱ ጉራጌ መሆኑ ነበር፤ እኛም በቅድሚያ ገምተን ነበር፤ ውሳኔዋ አሳዘነን፤ ዳግም እንድታስብበት ተነገራት። እኔ የመርጥኋት ግን ተገናኝተን በጉዳዩ እንድንነጋገር ቀጠሮ ያዝን፤ አይደርስ የለም ቀኑ ደርሶ አንድ ማታ አዛው ሆስፒታል ግቢ ውስጥ አንዲት ዛፍ ስር ቆመን ተገናኘተን፤ ተወያይተን አንድ እንሆን ዘንድ ተስማማን፣ የፍቅር ህ ሁ ተጀመረ። ይህ የሆነው በህዳር ወር 1948 ዓ. ም ነበር።

## ላጫት ካሰብኩት ልጅ ጋር ሽርሽር (First Date)

በዚያች ሰዋራ ቦታ ከዚያች ልጅ ጋር ቆመን ከተነጋገርን በኋላ ቁጭ ብለን ረዘም ላለ ጊዜ እንድንነጋገር ተቀጣጠርን። በሃሳባችን የመጣው ቦታ ቀበና ነበር። አንድ እሁድ ከሰዓት በኋላ ምንሊክ ሆስፒታል በራፍ ላይ ተገናኝተን የቀበናን ወንዝ ተሻግረን፡ አንዲት ገላጣ ቦታ ዛፍ ስር ቁጭ ብለን ዘመርን፤ አወራን።

ስለ ቦታው የምታውቀውን ነገረችኝ እኔም በዚያች ቦታ የገጠመኝን ነገርኳት። ገጠመኟ እንዲህ ነበር፡-

ከሁለት ዓመት በፊት የአዲስ አበባ ት/ቤቶች ስካውቶች በሙሉ በዚያች ቦታ የሦስት ቀን የጃምቡሬ በዓል ነበራቸው፡፡ እኔም በተግባረዕድ ት/ቤት የእስካውት አባል በመሆኔ ተካፋይ ነበርሁ፡፡ በየቡድናችን ካምፕ ተሰጥቶን፤ ምግባችንን እናዘጋጃለን፣ የእስካውት ልምምዶች እናደርጋለን፡፡ ትልቁ ችግር ውሃ ነበር፤ የቀበና ወንዝ እንኳን ለመጠጥ ለመታጠቢያም አይሆንም፤ የውሃ ችግራችንን ለመቅረፍ የማዘጋጃ ቤት በአባት አደጋ መኪና ውሃ እንደሚያመጣልን ተነገረን፡፡ ስንጠባበቅ ዉለን ማታ መኪናው መጣ፤ እኔ ዉሃ በጣም ጠምቶኝ ስለነበር የኔንና የጓደኞቼን ኮዳዎች ይዤ ለቡድኔ ዉሃ ለማምጣት ሄድሁ፡፡ እዚያ እንደደረስሁ የራሴን ኮዳ ሞልቼ እዚያው ግማሽ ኮዳ ያህል ጠጣሁ፤ ከዚያ በኋላ ኮዳዎቹን ሞልቼ ተመለስሁ። በማግስቱ ጠዋት ቁርስ ስናዘጋጅ ዉሃዉን ስመለከት ዉሃው ቀይ ነበር፡፡ "ይህንን ነው የጠጣሁት?" ብዬ የድንጋጤ ግርምት ያዘኝ።

ግቢ ከተመለስሁ በኋላ ታላቅ ቁርጠትና ተቅማጥ ስለጀመረኝ ወደ ክሊኒካችን ሄድሁ፤ መድሃኒት ተሰጠኝ፡፡ ሊሻለኝ አልቻለም፤ ወደ ማእከላዊ ክሊኒክ ተላኩሁ፤ ያ ክሊኒክ የባሰባቸው ታማሚዎች ተኝተው የሚታከሙበት ነበር፡፡ እዚያ ስደርስ በጣም ስለደከምሁ አስተኙኝ፡፡ ከሳምንት በኋላ ነበር ተሽሎኝ የወጣሁት።

እንዲህ እያጫወትኳት ከቆየን በኋላ አብረን ዘምረንና ጸልየን ወደ ቤት ጉዞ ጀመርን። እጅ ለእጅ ተያይዘን እየሄድን በትርፍ ጊዜያችን ምን ማድረግ እንደሚያስደስተን ተጠያየቅን፤ እኔ ፎቶግራፍ ማንሳት እንደምወድ ነገርኳት፤ እርሷ ፒያኖ/ኦርጋን መጫወት እንደሚያስደስታት ስትነግረኝ፡- "ግሩም ነው! እንዲህ ከሆነማ እሁድ እሁድ ቤተክርስቲያን ትጫወቺልናለሻ?!" አልኳት፤ "አይ ቅዳሜ ነው እንጂ እሁድ ቤተክርስቲያን አልሄድም" አለች፤ የሰባተኛ ቀን አከባሪ አድቬንቲስት መሆኗን እየነገረችኝ ነበር።





ስለ አድቬንቲስቶች የማውቀው ትንሽ ነበር፡፡ ሁለታችንም ተመሳሳይ እምነት መከተል እንደሚገባንና በየፊናችን እንድናጠና ውሳኔያችንንም እንድናሣውቅ ተስማምተን ተለያየን። የመጀመሪያው የፍቅር ሽርሽር በዚህ ተጠናቀቀ፡፡

***

# ምዕራፍ 4

## የውጪ አገር ተሞክሮ

### ባሕር ማዶ - ለትምህርት

በአዲስ የፍቅር ዓለም ውስጥ እየተንሳፈፍኩ ባለሁበት ወቅት አንድ ቀን የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር እኔና በከሪ አብዱላሂን ወደ ቢሮው ጠራን:: እኔ ራድዮ ሾፕ ረዳት ሆኜ ሳስተምር በከሪ ኤሌትሪክ ሾፕ ተመድቦ ነበር:: ዲሬክተሩ ቢሮ እንደ ገባን የምንቀመጥበትን ወንበር እያመለከተን:-

"የምሥራች! ፖይንት ፎር ለሁለታችሁም ስኮላርሺፕ ሰጥቷችኋል፤ በጣም ደስ የሚል ነገር ነው፤ ቢሆንም ግን እስቡበትና ነገ መጥታችሁ ውሳኔአችሁን እንድታሳውቁኝ" አለን።

እኔ ወዲያው "አመሰግናለሁ፤ ሌላ አቅድ አለኝ አልሄድም ልለው" ቃጥቶኝ ነበር። ይህን ለማለት የዳዳኝ ከጀመርኩት ትኩስ ፍቅር በተጨማሪ ከጓደኞቼ ጋር የወጠንነው አንድ ትልቅ ነገር ነበር:: ጉዳዩ እንደሚከተለው ነበር::

በየነ ጭጮ አይበሉ፣ ኃይሌ ወልደ ሚካኤል፣ እንግዳ አሰፋው፣ ንጉሴ አየለና ሌሎችም ጓደኞቻች ሆነን፣ በጊዜው የሚኖናይት ሚስዮን የሚያከናውነውን አይነት ሥራ ለመሥራት አገር በቀል የሚስዮን ተቋም ለመመሥረት እየተመካከርን ነበር:: ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ስለ መጀመር ነገር አስበነው አናውቅም፤ የወቅቱ ግንዛቤአችንም አያፈቅድልንም ነበር:: ምኞታችን ሚስዮኖች በትጋት የሚሠሩትን አይነት በጎ አድራጎት በተለይም በትምህርትና በሕክምና ዙሪያ ፕሮጀክቶችን መሥርተን እየሠራን ወንጌልን ማብሰር ብቻ ነበር:: ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ እንደሚባለው መሆኑ ነው::





መቼም የሚኖናይት ሚስዮናውያን የሙያ ስብጥር አስገራሚ ነበር:: አስተማሪዎች፣ ዶክተሮች፣ ህንጻ ገንቢዎች . . ወዘተ አሉበት:: እኛም:- የሚኖናይቶችን መሰል ፕሮጀክት በራሳችን ለማሳካት ገንዘብ ተገቢው ባለሙያ እንደ ሚያስፈልገን ተገነዘብን:: ጫካ መንጥረን ታላቅ የእርሻ መሬት ይኖረን ዘንድ አሰብን:: መቼም ዘመናዊ ግብርና ለማካሄድ ባለሙያ ያስፈልጋል፤ በየነ ጭጮ አይበሉ ጂማ እርሻ ኮሌጅን ለመቀላቀል ወስኖ ሲሄድ ለአላማችን መሳካት መሠረት እንደሚጥል አመንን::

ንጉሤና ኃይሌ አስተማሪ እንደሚሆኑ ታሰበ፤ እንግዳ በፓስተር ኢኒስቲትዩት ላቦራቶሪ ዉስጥ ይሠራ ስለነበር ሕክምና እንዲማር ታቀደ:: ከዋናዋናዎቹ ሙያዎች የጎደለው ግንበኛ ስለ ሆነ ያን ቦታ ለመሙላት በሚቀጥለው አመት ሕንፃ ኮሌጅ ገብቼ ግንበኝነት ለመማር ወሰንኩ:: እቅዳችን ይህ ነበር::

***

ዲሬክተሬ እድሉን ያበሰረን በጠዋት ነበር። ለምሳ ስሄድ ለኃይሌ ስኮላርሺፕ እድል እንዳገኘሁ ነገርኩት፤ ያን ጊዜ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት በግሉ እያጠና ስለ ነበር በጥልቅ ሳያስብ "ታዲያ ጥሩ ነዋ!" አለኝ፤ "እንዴ ምን ማለትህ ነው? ፕሮጀክታችንስ? በሚቀጥለው አመት ሕንፃ ኮሌጅ ልገባ አይደልም እንዴ?" ስለው "አይ እውነትህን ነው፣ ሰርዘው አለኝ።" ያን ለት ከሰዓት በኋላ ወደ ዲሬክተሩ ቢሮ ሄጄ "ስለ መረጣችሁኝ አመሰግናለሁ፣ ሌላ አቅድ ስለ አለኝ ላለመሄድ ወስኛለሁ:: እድሉን ለሌላ ስጡት" አልኩት:: በጣም ገረመው፤ ይህን እድል በመግፋቴ እንደ ተሳሳትሁም ሳይገምት አልቀረም።

ለበከሪ ውሳኔዬን ስነግረው፣ "አብደሻል እንዴ?!" አለኝ፤ (ያኔ የምንጠራራው በአንስታይ ፆታ ነበር) "ስኮላርሺፕ ሁላችን የምንፈልገው እድል አይደለም እንዴ? እንዴት ይህን እድል ትገፊአለሽ?" አለኝ። የበከሪ አስተያየት ሃሳቤን የከፈለው ቢሆንም ግን ለጊዜው በውሳኔዬ ጸናሁ:: እድሉ ለሌላ ሰው ተሰጠ::

ከቀናት በኋላ ንጉሤ ከናዝሬት መጣ፤ አዲስ አበባ በመጣ ቁጥር የሚያድረው ከእኔ ጋር ነበር፤ ጋደም እንዳልን፡-

"ሚሊ እኔ እኮ እስኮላርሺፕ ላለመሄድ፤ በወሰንከው ውሳኔ ደስተኛ አይደለሁም፤ እስቲ አስበው፣ እኛ ወጣቶች ነን፤ ይህ ያቀድነው ነገር ላይሳካ ይችላል፡፡ ደግሞም ሄደህ ተምረህ ብትመጣ ከመካከላችን ፈረንጅ አገር ተምሮ የመጣ አንድ ሰው ቢኖር እኮ ጥሩ ሊሆን ይችላል፤ ከሁሉም በላይ ግን እስኮላርሺፕ አለመሄድህ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እውቀሃል? ካወቅህስ እንዴት አወቅህ? ሲል ራሴን በራሴ እንድጠይቅ ኮረኮረኝ፡፡

የንጉሤ ጥያቄ የውሳኔዬን መሠረት እነቃነቀው፣ "የአምላከን ፈቃድ ተቃረንኩ እንዴ?" አልሁ፤ ይህ እቅዳችን ሳይሳካ ቢቀር በእዉነት እንደሚቆጨኝም አሰብሁ፤ መተኛት አቃተኝ፤ የጌታ ፈቃድ እንድሄድ ከሆነ አሁንም በር ሊከፍት ይችላል አልኩ፤ "ጌታ ሆይ ፈቃድህን ገፍቼ ከሆነ ይቅር በለኝ" ብዬ ጸለይሁ።

በማግሥቱ ጠዋት ዲሬክተሩ ቢሮ ሄጄ "ስለ ተሰጠኝ እድል እንደ ገና አስቤበታለሁ፣ መሄድ እፈልጋለሁ" አልኩት፤ በጣም ተቆጣ፤ "እድሉን ለሌላ ሰጥቻለሁ፣ አዝናለሁ" አለኝ፡፡ ልወጣ ስል፡- "እስቲ ቆይ፣ ዛሬ ከሰአት በኋላ ለተመረጡት ፈተና ይሰጣል፣ ፈተናው የተመረጡትን ችሎታ ለማየት ነው፤ የሚሆነውን ማን ያውቃል፤ አንተም ፈተናውን አብረህ እንድትወስድ ተጨማሪ የፈተና ወረቀቶች ይዘው እንዲመጡ አደርጋለሁ ተዘጋጅ" አለኝ።

ወደ ቢሮዬ ተመለስሁና "ጌታ ሆይ ፈቃድህን በእርግጥ ሳላውቅ እልፈልግም በማለቴ አዝናለሁ፡፡ እንድሄድ ከፈለግህ በፈተናው ጥሩ ውጤት እንዳመጣ እርዳኝ፤ እንዳልሄድ ካልፈለክ 3 + 4= 9 ብዬ እንድመልስ አድርገኝ ብዬ ጸለይሁ። ፈተናውን ከወሰድኩ በኋላ በውጤቱ የእግዚብሔርን ፈቃድ መገለጥ መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡

የፈተና ውጤቴ ጥሩ እንደነበርና ወደ አሜሪካ እንድምሄድ ተነገረኝ፡፡ እንድንሄድ የተመረጥነው ሰባት ነበርን። በከሬ አብዱላሂና አበበ ሃይሉ ከኤሌትሪክ ሾፕ፣





አረፋይኔ ካሳሁን፣ ከፋውንደሪ ሾፕ፣ እሰፋ ከበደ ከማሺን ሾፕ፣ ዮሐንስ ወልዴ ሥላሴና ይልማ ደስታ ከሞተር ሾፕ፣ እኔ ከራዲዮ ሾፕ ነበርን። በማለፌ ብቻ ሳይሆን የእግዚብሔርን ፈቃድ የሕይወቴን አቅጣጫ ሲቀይሰው መረዳቴ ደስታዬን እጥፍ አደረገው፡፡

ለመሄድ ዝግጅት ተጀመረ፤ ልዩ ልዩ ሰዎች ከፖይንት ፎር እየመጡ ስለአሜሪካ ኑሮ፣ ስለ ፖለቲካው፣ ስለ ጥናት ዘዴ አስተማሩን። በተለይ ያተኮሩት እንግሊዝኛ ቋንቋችንን ማሻሻል ላይ እና የመረዳት ችሎታ (comprehension) ላይ ነበር። በዚህ ኮርስ የምናነበውን ይሰጡንና አንብበን ምን ያህል እንደተረዳንና እንደምናስታውስ ይፈትኑናል። ኮርሱ በሚሰጥበት ወቅት በአፍላ የፍቅር ስሜት ውስጥ የነበርኩበት ጊዜ ስለነበር ተቸግሬ ነበር፡፡ የተሰጠንን ንባብ አንብቤ ጥያቄ ለመመለስ በማደርገው ዝግጅት ውስጥ ልጂቷ በሃሳቤ ትመጣብኝ ስለ ነበረ ጥሩ ውጤት ማምጣት ተሳነኝ፤ ድካሜን እንዳሻሽል ተመከርኩ።

***

## ዝግጅትና ጉዞ

ወደ አሜሪካ ለመሄድ ዝግጅታችን ተፋፋመ፡፡ በዚያን ዘመን ወደ ውጭ የሚላክ ተማሪ የትምህርት ሚኒስቴር የሚያስፈልገውን ሁሉ ይገዛለት ነበር፡፡ ሁለት ሙሉ ልብስ፣ ሸሚዞች፣ ከራባቶች፣ የውስጥ ልብሶች፣ ካቦርታ፣ ባርኔጣ፣ እንዲሁም ልብሶቻችንን የሚይዝ ሻንጣ ተገዛልን፡፡ ያኔ መንግሥት የገዛልኝ ሰማያዊ ኮትና ሱሪ በአሜሪካ ቆይታዬ ከተጠቀምኩበት በኋላ ከሶስት አመት በኋላ ወደ አገር ቤት ተመልሼ ለሠርጌም ተጠቅሜበታለሁ፤ የጥራቱን ልክ ያሳያል፡፡

ለፓስፖርት የሚሆን ፎቶግራፍ ስነሳ ኮፒውን በርከት አድርጌ አሳትሜ ለፍቅረኛዬና ለጓደኞቼ ሰጠሁ፡፡ እርሷንም ፎቶ ጆርጅ ወስጄ አስነሳኋት፡፡ የፍቅር ጓደኛዬን ፎቶ በኪሴ መያዜ ኩራት ቢጤ ፈጠረልኝ፡፡ ለማውቃቸው ሁሉ የፍቅር ጓደኛዬን ፎቶግራፍ ተመልከቱ ብዬ ለመፎከር በቃሁ። በፉከራዬ

መሐል የሃይማኖት ልዩነታችን መልሰ እንዳላገኝ ሳለብ ሰጋት ወረር የሚያደርገኝ ቢሆንም መልካም ምላሽ እንደማገኝ ተስፋ አድርጌ ፋክራዬን ቀጠልኩ::

ዝግጅታችንእንደተጠናቀቀ አብረን የምንጓዘው ሰባታችንም ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ሄደን ጃንሆይን ተሰናብተን:: ጃንሆይም "በሉ አንግዲህ ተምራችሁ መጥታችሁ አገራችሁን የምታገለግሉ ሁኑ" በማለት ንጉሣዊ ምክራቸውን ሰጥተው እሰናበቱን።

## የአየር ጉዞ ትዝታዬ

የካቲት 4/1948 ጠዋት በሶስት ሰአት ኮንቬር በሚባል ባለ ሁለት ሞተር አይሮፕላን ተሳፍረን ጉዞ ጀመርን:: አዋሽ አርፈን ቤንዚን ከሞላን በኋላ ወደ አሥመራ መብረር ጀመርን:: ወደ አስመራ ለንበር፣ ቁርሰ ቀረበልን። ቁርሱ ዳቦ፣ ቅቤ፣ ኮርንፍሌክስና ማርማላታ ነበር፤ ኮርንፍሌክሰ በልቼ አላውቅም ነበር። መሞከሩ አይከፋም በማለት አንደ ቆሎ አየቃምኩ ቆረጠምኩት:: ይሀቺ የቅንጦት ነች አልኩ::



በ1948 .ዓ.ም ወደ አሜሪካ ስሄድ የሸኙኝ





ዳቦውን አንስቼ ቅቤና ማርማላታ ቀብቼ ልበላ ስል ጎኔ ያለው አበበ ሃይሉ፡ "አፈር ብላ አናቶቻችን አራሳቸውን የሚቀቡትን ያልተነጠረ ቅቤ እንዴት ትበላለህ?" አለኝ፡፡ አሣቀኝ የኬንያ ቅቤ አየቀቡ ዳቦ መብላትን ከነበየን ተምሬአለሁና፤ ወሎዬው አበበ ዳቦ በቅቤ ቀብቶ በልቶ እያውቅም ነበር፤ የተሻለ የሰለጠንኩ አይነት ስሜት ተሰማኝ።

ገና ርቄ ሳልሄድ ፍቅረኛዬ ትናፍቀኝ ጀምራለች:: ቁርሰ ከበላን በኋላ በፊታችን ባለው ቦርሳ ዉሰጥ የሚነበቡ ጋዜጣዎች፣ ደብዳቤ መጻፊያ ወረቀቶችና ካርዶች እየሁ፤ እንዷ ወረቀት ላይ ለፍቅረኛዬ ደብዳቤ ጻፍሁና አስመራ ላይ ሰንደርሰ እንዲልኩልኝ ሰአሰተናጋጆቹ ሰጠኋቸው:: በደብዳቤ ስሜቴን ማስፈር በመቻሌ ትንሽ ቀለል ብሎኝ ከእሰመራ ተነሰተን ጉዞአችንን ቀጠልን::

ፖርት ሱዳን አርፈን ከአይሮፕላኑ ወጣ ስንል የውጪው አየር ሙቀቱ ያቃጥላል፤ አይሮፕላኑ ከንፍ ስር ቆመን ቤንዚን ተሞላና እንደገና መብረር ጀመርን:: ካይሮ ከምሽቱ አንድ ሰአት ደርሰን አረፍን:: ከአዲስ አበባ ከተነሳን ከ12 ሰዓት በኋላ መሆኑ ነው:: እዚያ ወራጅ መንገዶችም ነበሩ፤ አነርሱ ከወረዱ በኋላ ቀጣይ መንገደኞችንም እንድንወርድ ተነገረን:: ጀለቢያ የለበሰ አንድ ሰው ወደ አንድ ትልቅ አዳራሽ ዉስጥ አሰገብቶ ዳግም እሰኪመጣ ድረሰ አንድንጠብቀው አዞን ሄደ:: ትራንዚት ላውንጅ መሆኑ ነው::

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ወደ እቴንስ ጉዞ ቀጠልን:: በሜዲተራኒያን ባህር ላይ አየበረርን እያለ ሌሊት ሰለ ሆነ ወደ ወጭ ስንመለከት የአውሮፕላኑ ሞተር ቀይ ፍም ይመሰላል፤ ከቀይነትም አልፎ ወደ ነጭነትም ተቃርቧል:: የሚቃጠል መሰለኝ፤ ከተቃጠለ ባሕር ዉስጥ ጠልቀን መቅረታችን ነው፤ "የአፀደ እምልክ ጠብቀኝ" አልሁ:: በአኔ ሰአት ከምሽቱ ሰባት ሰአት ሲሆን እቴንስ ገባን:: እፎይ! በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ እየር መንገድ የሚሄደው እሰከ አቴንስ ብቻ ነበር።

አቴንስ አንደ ደረሰን ወደ ሆቴል ተወሰድን:: አትክፍሉም ተባልን ገረመን:: ሆቴል ውሰጥ በየክፍሉ ሁለት ሁለት ተደለደልን:: አኔና አረፌ አይኔ ካላሁን አንድ ክፍል ተመደብን:: ክፍል አንደገባን ክፍሉን ቃኘሁት፤ እንዲህ ያለ

የመኝታ ክፍል አይቼ አላውቅም። ሁለት አልጋ፣ ወንበሮች፣ መታጠቢያ ክፍል፣ የእጅ መታጠቢያ፣ የገላ መታጠቢያ ገንዳ አለው፡፡ ከአዲስ አበባ ከመነሳቴ በፊት ፍል ዉሃ ሄጄ አንደኛ ማዕረግ ታጥቤ ነበር፤ ይሄ ግን ልዩ ነው፤ ሳሙናና ፎጣ አለ፡ ባኞውን ውሃ ሞልቼ ታጠብሁ፡፡ እንዲህ ስታጠብ ለመጀመሪያ ጊዜዬ ነው፤ አዲስና ዘመናዊ የኑሮ ልምምድ ጀመርሁ ማለት ነው። ከመተኛታችን በፊት እንደ ልማዴ መጽሐፍ ቅዱሴን ላነብ ገለጥሁ፤ አረፋይኔ እንዲሳተፍ ጠየቅሁት፤ በደስታ አለኝ፤ አነበብኩና ለሁለታችንም ለጓደኞቻችንም ጸለይሁ፡፡ አረፋይኔ በጣም ደስ አለው፤ በቃ አንተ ለኔ ልዩ ጓደኛዬ እንድትሆን እፈልጋለሁ አለኝ፤ እንዳለውም ሆንን።

***

በማግስቱ ወደ ኒውዮርክ የሚወስደን የTrans World Air lines(TWA) አይሮፕላን የሚነሳው ከሰአት በኋላ በዘጠኝ ሰአት እንደሆነ ተነግሮን ስለነበር ጠዋት የአቴንስን ከተማ ለመጎብኘት ወሰንን፡፡ ቁርስ ከበላን በኋላ መረጃ ጠያይቀን የአቴንስ ከተማን ለመጎብኘት ለታክሲ ገንዘብ ስለ ሚያስፈልገን ወደ ባንክ ሄድን፡፡

ባንክ ለመሄድ ለታክሲ ምን ያህል እንደሚያስከፍል ከሆቴላችን ለዎች ግምት ተሰጥቶን ሁለት ታክሲ ተከራይተን ወደ ባንክ ጉዞ ጀመርን፡፡ ታክሲዎቹ የከተማዋን ዋና ገጽታ አስጎበኝተው መለሱን፡፡ የጠየቁን ክፍያ ግን ከተነገርን በጣም ብዙ ነበር፡፡ ለማስቀነስ መከራከር ጀመርን፤ ከርከሩ እንደ ተጋጋለ እዚያ አገር በመማር ላይ ያለ ኢትዮጵያዊ "እነኚህ ያገሬ ለዎች አይደሉም እንዴ?" በማለት ቀርቦ አነጋገረን፤ ጉዳዩን አስረዳነው፡፡ በጣቱ እያመለከተ "ሆቴላችሁ እኮ ያ ነው! በእግራችሁም መምጣት ትችሉ ነበር" ብሎ ታክሲ ነጂውንም ወቅሶ፤ ክፍያውን ሸፍኖልን፤ ታክሲ ነጂውን አሰናበተልን። አቴንስን አስጎበኘን። የዚያን ሰው ደግነት አልረሳውም፡፡ እዚያው አቴንስ ነበር እኔና በከሪ ካሜራ የገዛነው፡፡ ምሳ ከበላን በኋላ ወደ አይሮፕላን ጣቢያ የሚወስደን አውቶቡስ መጥቶ ወሰደን።





***

ከአቴንስ በዘጠኝ ሰአት በባለ አራት ሞተር አይሮፕላን ወደ ኒውዮርክ ጉዞ ጀመርን። መጀመሪያ ሮም አርፈን ከዚያም ወደ ጀኔቭ በረርን፡፡ ጀኔቭ አይሮፕላን ማረፊያ ስንደርስ ብርዱ ጆሮ የሚበጥስ ነበር፣ መሬቱ ነጭ ነበር። ስረግጠው ነጭ አሸዋ የምረግጥ መሰለኝ፡፡ ጎንበስ ብዬ የረገጥሁትን ሳነሳ እጄ ላይ ሟሸሸ "በረዶ ማለት ይህ ነው?" ነበር ያልኩት።

ትራንዚት ላውንጅ ስንዘዋወር አንድ የጠረጴዛ ሰአት ገዛሁ፤ ወደ ፓሪስ እንደምንበር ተነግሮን ጉዞ ጀመርን፡፡ አይሮፕላን ላይ እንደወጣሁ እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡ ብንን ስል አጠገቤ የተቀመጠውን በከሪን "ፓሪስ ደረስን ተነስ" ስለው፡ "እይ እንቅልፋም ፓሪስማ አርፈን፤ አሁን ሎንዶን ልናርፍ ነው" አለኝ፡፡

ሎንዶን አርፈን አትላንቲክን ከማቋረጣችን በፊት ሻንን፣ ኤይርላንድ አርፈን አትላንቲክን ማቋረጥ ተያያዝነው፡፡ ቀን ቢሆንም ከበታቻችን ያለውን ባህር ማየት አልቻልንም፤ የምንበረው ከነጭ ጉም በላይ ስለ ነበር፡፡ የተነደፈ የፈትል ጥጥ ላይ የምንበር ነበር የመሰለኝ፡፡

በጣም ያምራል፤ ስምንት ሰአት ከበረርን በኋላ ጋንደር ካናዳ አረፍን፡፡ ከዛም ወደ ቦስቶን መብረር ጀመርን፡፡ በጣም አቅለሸለሸኝ፤ በከሪ "ባትታገሺ ይሻላል" ስላለኝ ለቀቅሁት፡፡ ቀለለኝ፣ ጉሮሮዬን የሚያጥብልኝ እንደሲናልኮ ያለ የሚከረከር መጠጥ ፈለግሁ፡፡ በስቶን እንደ ወረድን መግቢያው ላይ ምናምን የተለቀለቁ ወይም ተሰንጥቀው ስጋ ብጤ ያላቸው ዳቦዎች ጠረጴዛ ላይ ተደርድረዋል፡፡ የቺዝ፣ የሥጋ ሳንድዊቾች መሆናቸው ነው፤ ስቅምስቸው ምንም አልጣሙኝም፤ እኔ ያማረኝ እንደሲናልኮ ያለ መጠጥ ነበር፡፡ የሚበላም ከሆነ ኮስተር ያለ ነገር ቢሆን ነበር የፈልግሁት፡፡ ከበከሪ ጋር ስንንጎራደድ አንድ ትልቅ ሳጥን አይነት ነገር ቆሞ አየን፤ ጎኑ ላይ ሲናልኮ የምትመስል ትንሽ የጠርሙስ ሥእል አለባት። ጠጋ ስንል "ይህቺን መጠጥ ኪንግ ጆርጅ ባር አይቼአታለሁ" አለኝ በከሪ፡፡ አምስት ሳንቲም ጨምሩ የሚል ምልክት አየን፡፡

ሚስ ስንይደር (Miss Snyder) ከመነሳቴ በፊት የ 5፣ 10፣ 25 ሳንቲም አይነቶች ለናሙና እንዲሆነኝ ስጥታኝ ነበር፡፡ ከነኚህ ውስጥ የ5 ሳንቲሟን ስንጨምር አንድ ጠርሙስ ኮካ ኮላ ብቅ አለች። በጥርሲ ልከፍት ስል በከሪ "ቆይ እስቲ እነኚህ ሰዎች መክፈቻም ሳያዘጋጁ አይቀርም" ብሎ ስንመለከት open here የሚል አገኘን፡፡ ከፈትን፤ መጀመሪያ በከሪ ቀምሶ ግማሽ ያህል ከጠጣት በኋላ "እንደ ሲናልኮ ያለች ጥሩ ነች" አለኝና ሰጠኝ፡፡ ጉሮሮዬን የሚፍቅልኝ የፈልግሁት አይነት መጠጥ አገኘሁ፡፡ ኮካ ኮላ ነበረች፣ ሥልጣኔው ቀጠለ ማለት ነው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጉዞ ወደ ኒው ዮርክ ቀጠልን፡፡ በአገሩ ሰአት አቆጣጠር ልክ በዘጠኝ ሰአት የካቲት 6 ቀን 1948 ዓ ም (February 16. 1956) ኒው ዮርክ ገባን። ኒው ዮርክ ስንደርስ የፖይንት ፎር ወኪሎች ተቀብለው በሌላ አይሮፕላን ወደ ዋሺንግቶን ሰደዱን፡፡ ዋሺንግቶን ደግሞ ሌሎች የፖይንት ፎር ሰዎች ተቀብለው NEW AVENUE HOTEL ወስደው ለእያንዳንዳችን ክፍል ተሰጠን፡፡

## ዋሽንግተን ዲሲ

በማግስቱ መጥተው ወደ አንድ ቦታ ወስደው ለሚቀጥሉት 15 ቀናት የተዘጋጀልንን መርሐ ግብር አስታወቁን፡፡ በተከታዩ ቀናት ለምግብና ለሚያስፈልገን ጥቃቅን ነገር የምንጠቀምበት ገንዘብ ተሰጠን። በየቦታው መመገቢያ ቦታዎች እንደሚገኙ፣ መመገቢያ ቦታዎችም ሬስቶራንት ወይም ካፌቴሪያ እንደሚባሉ ተነገረን።

የአስራ አምስቱ ቀን ፕሮግራም ስለ አሜሪካ ፖለቲካ አመራር፣ ስለ ባህልና ዋሺንግቶንን በሰፊው መጎብኘት ነበር፡፡ ኮንግረስንም አሳዩን፡፡ በጣም ያስገረመን ኮንግረስ ውስጥ አንድ ሃሳብ የሚያቀርብ አማካሪ ቆሞ ይለፈልፋል፤ የሚያዳምጡት ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው፤ ሌሎች መጽሐፍ ወይም ጋዜጣ ያነባሉ። ብዙ ባዶ መቀመጫም ነበሩ፤ "ይህ ለምን ይሆናል" ብለን ስንጠይቅ፤ አያንዳንዱ አማካሪ ረዳቶች እንዳሉት፣ እነኚህ ረዳቶች በኮንግሬስ የሚደረጉትን ዲስኩሮች አንብበ ሌሎች አማካሪዎችና ዉጭ ያሉ ‐የህዝቡን ስሜት





የሚያንጸባርቁ ጋዜጠኞች የሚሉትን ሁሉ ተከታትሎ የተባለውን አጠርጠር አድርገው እንደሚያቀርቡላቸው ነገሩን።

***

## በአሜሪካ የመጀመሪያው ወዳጄና መስተንግዶ

ከኢትዮጵያ ከመነሳቴ በፊት፡ ሚስ ስናይደር እኔን ለማስተዋወቅ ዋሺንግቶን ዉስጥ ለሚኖር ኤድ ሜትዝለር (Ed Metzler) ለሚባል ሰው ደብዳቤ ጽፋልኝ የስልክ ቁጥሩንም ስጥታኝ ነበር፡፡ የሚስ ስናይደር ደብዳቤ በአጭሩ ደደር ሚኖናይት ሚሺን ተማሪ እንደነበርሁ፤ አዲስ አበባ ከእነርሱ (ሚኖናይቶች) ጋር እንደማመልከ የቅርብ ግንኙነት እንዳለን የሚገልጽ ነበር" ዋናው ነጥቧ ግን ከወራት በፊት ጥምቀት መውሰዴን ማሣወቅ ነበር። እውነቷን ነው፤ የተጠምቅሁት ነሐሴ 6/1947 ከስድስት ወር በፊት ነበር፤ ምኞትዋ እርሱና የእርሱ ብጤዎች እንዲጠነቀቁልኝና በሚያስፈልገኝ ሁሉ እንዲረዱኝ ነው።

ኤድ የሜኖናይት ቤተ ክርስቲያንን አቋም ለማስረዳት፣ ቤተ ክርስቲያኗን ለመወከል በኤም.ሲ.ሲ (MCC: Mennonite Central Committee) የተመደበ ሰው ነው፡፡ ጊዜ ሲመችኝ ደወልኩለት፤ "ታዲያ በደንብ እንድንተዋወቅ ወደ ቤታችን ብትመጣ ደስ ይለኛል፤ መቼ መጥቼ ልውሰድህ?" ሲል መለሰልኝ፤ ለመገናኘት ቀጠሮ ያዝንም፡፡

በቀጠሮአችን መሠረት ኤድ መጥቶ ወሰደኝ፤ ቤት እንደደረስሁ ሚስቱ በታላቅ ፈገግታ "እንኳን ወደ ቤታችን በደህና መጣህ" በማለት ተቀበለችኝ፡፡ የመጀመሪያ መስተንግዶዋን ለሰላሳ ሰጥታን ከጠጣን በኋላ ባለቤትዋ ወደ ሱቅ ሄዶ አንዳንድ ነገሮች እንዲገዛላት ጠየቀችው፤ ትንሽ ልጁን ይዞ ሊወጣ ሲል "አብረኸን መሄድ ትፈልጋለህን?" አለኝ፤ አብረን ሄድን፡፡ የሄድነው ወደ ሱፐር ማርኬት ነበር፡፡

ከውጭ ሳየው ትልቅ አዳራሽ ነው፡፡ በሩን የሚከፍትልን ዘበኛ የለውም፤ ልንገባ ስንል በሩ ተከፈተልን፤ ዘበኛ የለ ማን ከፈተው?! ብዬ በግርምት ዙሪያየን ብቃኝም ማንንም አላየሁም፡፡ ግራ እንደገባኝ ወደ ውስጥ ዘለቅን፤ እንደገባን

ከበሩ አጠገብ አንድ ከፍት ጋሪ አንሉቶ እየገፋ የሚፈልገውን እቃ ዋጋ ሳይጠይቅ ከየመደርደሪው እያነሳ ጋሪው ዉስጥ አድርጎ በራፍ አጠገብ ወዳሰች ገንዘብ ተቀባይ ሔደ:: ገንዘብ ከፈለና የገዛው በትልቅ የወረቀት ኬሻ ተደርጎለት ይዞ ሲወጣ አሁንም ያ በር ወለል ብሎ ተከፈተለት፤ ለንገባም ለንወጣም በሩ ሳንነካው መከፈቱ ገረምኝ፤ ግሩም ነው! እንዲህ ነው ስልጣኔ! አልሁ::

ይህን ገጠመኝ ስጽፍ በቅርቡ አሜሪካ የሄዱ አዛውንት የገጠማቸው ተብሎ የሰማሁትን ልጨምር፡ አዛውንቱ ከልጃቸው ጋር እንዲህ ያለ በር ያላቸው ሱቆች ይሄዳሉ፣ በሩ አጠገብ የከፈተላቸውን ሰው ቢፈልጉ ያጡታል ግራና ቀኛቸውን ያዩና ባርኔጣቸውን ከፍ አድርገው አጅ ይነሳሉ:: ድርጊታቸው ያስገረመው ልጃቸው አባዬ ለምን እንዲህ አደረክ ቢላቸው "ልጄ በሩን የከፈተልንን ሰው አላየሁትም እርሱ ስለሚያየኝ አጅ በመንሳት ላመስግነው ብዬ ነው" አሉት::

አራት አየበላን ስለ አስተዳደጌ፣ ስለ ኢትዮጵያ፣ ከሚኖናይቶች ጋር እንዴት እንደ ተዋወቅሁ፣ ወደ አሜሪካ እንዴት ልመጣ እንደ ቻልሁ ... ወዘተ አወራን፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየሄድኩበት ቤት የማወራው ርዕሰ ይሄው ነበር:: ከርስትና አሜሪካ ከመግባቱ በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንደ ገባ፣ ስለ ስልጣኔያችን፣ ፊደል እንዳለን፣ ብዛታቸዉም 231 እንደ ሆነ፣ ለፔሊንግ ማጥናት እንደማያስፈልገን አነግራቸዋለሁ:: በተለይ ልጆች የፊደሎቻችንን ብዛት ሲሰሙ ዋው! ይላሉ፤ MARY የሚለውን በአማርኛ "ሜሪ" ብዬ ጽፌ ሳሳያቸው ለምን ሁለት ፊደል ብቻ ሆነ? ይሉኛል::

ከአዲሱ የአሜሪካ ቤተሰብ ወዳጆቼ ጋር አራት ከበላን በኋላ ሪችሞንድ ካሉ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዬ ከሚስተር ዌንገር ጋር በቴሌፎን አገናኙኝ:: በጣም ደስ አለኝ፤ በአይን ላያቸው ስለ ፈለግኹ እዚያው ቁጭ ብዬ አሉበት ት/ቤት በአውቶቡስ ሄጄ እንዳያቸው አቅድ ወጣ:: ጉዞው የአራት ወይም የአምስት ሰአት እንደሚሆን ተነገረኝ። የሚቀጥለው ሐሙስ የእረፍት ቀኔ እንደሆን ለለማውቅ በዚያ ቀን ሄጄ ላያቸው ወሰንሁ:: ግሬሃዉንድ አውቶቡስ በሰንት ሰአትና የት





እንደምሳፈር፣ አድራሻው ተሰጥቶኝ ተሳፈርሁና ሄድሁ:: ከዛ በኋላ የአውቶቡስ ጉዞ ደምበኛ ሆንኩ::

## ዊሊያምስፖርት ቴክኒካል ኢንስቲትዩት

የአስራ አምስት ቀኑ ፕሮግራም ሲያልቅ ወደ ዊሊያምስፖርት ቴክኒካል ኢንስቲትዩት ተላክን፤ የሄድነው በባቡር ነበር:: ሌሎች መሰል ተቋማት አዲስ ተማሪ የሚቀበሉት በመስከረም ወይም በጥር ወር ሲሆን ይህኛው ግን አዲስ-ገቦችን በማንኛውም ጊዜ የሚቀበልበት አሠራር ነበረው:: ለዚህም ነበር ወደዚያ የተላክነው::

የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ባቡር ጣቢያ ድረስ መጥቶ ተቀበለንና ወደ መኖሪያ ቤታችን ወሰደን:: ከእኔ ቀደም ብሎ መጥቶ ስለ ራዲዮ ከሚማረው ከአሰፋ ገብረ ጊዮርጊስ ጋር ተገናኘን:: ኑሮዬን ተረጋግቼ በዊልያምስፖርት ፔንሲልቫኒያ (Williasport Pensylvania) ጀመርኩ። እርግጥ ነው - ገና ከመጀመሪ ቤተሰቦቼና አገሬ ይናፍቁኝ ነበር:: ከፍቅረኛዬ ጋር የደብዳቤ ልውውጣችንን



የዊሊያምስፖርት ኢንስቲትዩት ዳሬክተር ባቡር ጣቢያ ድረስ መጥተው ሲቀበሉን

ቀጥለናል ምን ወስና ይሆን? ብዬ አስብና ደብዳቤ አስከትጽፍልኝ በጉጉት አጠብቃስሁ፡፡

ዊሊያምስፖርት ስኖር ወደ ላንካስተር እየሄድኩ ብዙ የሜኖናይት ቤተ ክርስቲያኖችን ጎብኝቼአስሁ፤ በበዙ ቤተ ክርስቲያኖች ምስክርነቴን ሰጥቻስሁ፤ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት አብዛኞቹ ሚስዮኖች የሄዱት ከዚያ ስስሆነ ቤተሰቦቻቸውና የነበሩበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይጋብዙኝ ነበር። "የላካችኋቸው ሚሲዮኖች ፍሬ ነኝ" ስላቸው ደስ ይላቸው ነበር።

***

ዊሊያምስፖርት ስኖር አንድ የማልረሳው ነገር ሆነ፤ አንድ ቀን ሊነጋ ሲል በጣም ሆዴን ቆረጠኝ፡፡ የርሃብ ቁርጠት መስለኝ፤ ማታ ጥሩ አራት እንደበላሁ አስታወስሁ፤ ቢሆንም ረሃብ ስለመሰለኝ ሲነጋ ተጣጠብሁና ምግብ ወደ ምንበላበት ሄድሁ፡፡ የመጀመሪያው በመሆኔ አስተናጋጁ "My Boy! you are early (ልጄ በጧት መጣህ)" አለኝ፡፡ እንቁላል ጥብስ አዘዝሁና ልበላ ስል አቃተኝ፤ ቁርጠቱ የሚለቀኝ ስበላበት ነው በማስት በግድ ግማሹን በላሁና ወደ መኝታ ቤቴ ተመልሼ ጋደም አልሁ፡፡ የበላሁት አስመለሰኝ፤ ወደ ት/ቤቱ ከሊኒክ ሄድሁና ስነርሷ ስነግራት፡ ይህን ዋጥ፡ ያሽልሃል ወይም ያብስብሃል አለቺኝና እዚያ አልጋ ላይ ጋደም በል.አስቺኝ ፣ ውጪ ተጋደምሁ፡፡ ምንም አልተሻስኝም ወደ ሆስፒታል ላከቺኝ።

አስቸኳይ እርዳታ ወደሚገኝበት ክፍል ነበር የተወሰድኩት፡፡ የመረመረኝ ዶክተር ሌላ ዶክተር መጥራት አስብኝ፣ መተኛት አስብህ ብሎ አራት በሽተኞች በሚተኙበት ክፍል ተወሰድሁ፡፡ ሌላ ዶክተር መጣና መረመረኝ፤ ትርፍ አንጀት (appendicitis) ነው፣ አፐራስዮን መሆን አስብህ፣ ምግብ በልተሃል?" አስኝ፤ "ቁርሴን በልቼ ነበር፡ ግን አስመለሰኝ" አልኩት፤ "ምሳ አትስጡት ከስአት በኋላ አፐራስዮን እደርገዋለሁ" አለና ሄደ። አፕራሲዮን የሚለውን ውሳኔ ስስማ ደንገጥ አልሁ፡፡ በሰው አገር ብቻዬን አፕራሲዮን መሆን ቢያስፈራኝም ህመሙ ስለበዛብኝ በአፕራሲዮኑ ተስማምቼ መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡





ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንዲት ነርስ ፎርም ልታስሞላኝ መጣች፤ "ስምህ ማነው? መቼ ተወለድህ? አድራሻህ? የቅርብ ዘመድ ስም?" አስች፤ "የት የሚኖር" ስላት "በዚህ አድራሻ" አለች፤ "እንኳን በዚህ አድራሻ በመላው አሜሪካ ዘመድ የለኝም አልኳት"፤ "እረ ስመሆኑ ለምን ፈለግሽው" አልኳት፤ "እንደምታውቀው አፐራስዮን ልትሆን ነው፤ አፐራስዮን መሆን ቀላል ነገር አይደለም፤ ማን ያውቃል አንድነገር ብትሆን ጫማህን ልብስህን የምንሰጠው ሰው መኖር አለበት" አስች፤ "ትሞት ይሆናል ማለትሽ ነው?" አልኳት፤ "አፐራስዮኑ ቀላል ነው፡ ግን . . ." አስች፡፡ የቅድሙ ፍርሃቴ ተመልሶ መጣብኝ፤ ፍርሃቴን ወደጎን ብዬ ከህመሜ ጋር እየታገልኩ መውጫ መንገድ ማሰብ ጀመርኩ "የጓደኛን ስም ልስጥ አችላለሁ?" አልኳትና የአስፋ ገብረ ጊዮርጊስን ስም ስጠኋት።

አርሷ ከሄደች በኋላ ማሰብ ጀመርሁ፤ "እንዴ! እሞት ይሆን?" ብዬ በሰፊው አስብኩ። ብሞት እናቴ 'እነኚህ ፈረንጆች ልጄን ገደሉብኝ ብላ ታዝናለች' ብዬ አስብሁ፤ ሁሉን ነገር ትቼ ብሞት የምሄደው ወደ ኢየሱስ መሆኑን ሳስብ ፍርሃቴ ጭንቀቴ ጠፋና መፍራት አቆምኩ ፡፡ አንድ ነገር ግን ቅር አለኝ "እንዴት ስአንድ ሰው እንኳን ስለጌታ ኢየሱስ ሳልመስክር እሞታስሁ? " ቅሬታዬ ወደ እምነት ተስወጠ "ይህን አገልግሎት ሳልፈጽም አልሞትም" የሚል እምነት ሞላብኝ፡፡ ይህን ሁሉ ሃሳብ ሳወጣና ሳወርድ ዶክተሮቹ ተዘጋጅተው ጨርሰው አፕራሲዮን ተደረኩ፡፡ እንደፈራሁት ሳይሆን ቀርቶ በህይወት ነቃሁ፡፡ በጥቂት ቀናት ውስጥ ፍጹም ጤነኛ ሆኜ ተነሣሁ፡፡

***

ዊሊያምስፖርት ስንኖር ከአሜሪካ አኗኗር ጋር ተዋወቅን። እኛ ስባታችን አንድ ቤት ዉስጥ በህብረት እንኖር ነበር፡፡ ሁሉን በህብረት እናደርጋስን ቤታችን አጠገብ ባስች ትንሽ ምግብ ቤት እንመገባስን፤ ስመኖሪያና ምግብ ስባለ ምግብ ቤቱ እንከፍላስን፣ ቅዳሜም ከሰአት በኋላ ተያይዘን ወደ ከተማ እንወጣስን፡፡

ታዲያ ቅዳሜ ወደ መሃል ከተማ ስንጓዝ እጅ ስእጅ ተያይዘን ስንሄድ ሰዎች ይገረማሉ፤ ስምን እንደሚገረሙ አናውቅም ነበር። አሁን ሳስበው በዚያን

ጊዜ ብዙ ባይወራም ቅሉ እጅ ለእጅ መያያዛችንን ከግብረ ሰዶማዊነት ጋር ሳያያይዙት አይቀርም፡፡ በተረፈ በርከት ያሉ ሲኒማ ቤቶች ስላሉ ጓደኞቼ ወደ ሲኒማ ቤት ሲሄዱ እኔ ብቻዬን አንዱት የክርስቲያን የመጽሐፍና የሙዚቃ መደብር ስላለች ወደ እዚያች ሄጄ የሙዚቃ ዲስኮች ወይም መጻህፍት እመርጥና ገዝቼ እመለሳለሁ። የክርስትና ህይወቴን የገነቡ ብዙ መጻህፍትም ገዝቼአለሁ። እሁድ እሁድ ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ። በዊሊያምስፖርት፣ ፔንሲልቫኒያ በነበርኩበት ከተማ የሜኖናይት ቤተ ክርስቲያን ስላልነበረ ወደ ሞሪስታውን ከተማ የሚወስዱኝ ቤተሰቦች ነበሩ፡፡ ወደ ላንካስተር ካውንቲ ብዙ ጊዜ ተጋብዤ ሂጃለሁ።

በተረፈ በእረፍት ጊዜዬ ለቤተሰቦቼና ለፍቅረኛዬ ደብዳቤዎች መልስ እጽፋለሁ፡፡ ከፍቅረኛዬ ጋር ወደ ፊት በህብረት አብሮ ለመኖር የሚያስችለንን የሃይማኖት አንድነት ጉዳይ እዚህ አሜሪካ ከመጣሁ በኋላ ብዙ ተጻጻፍንበት፤ ስለአድቬንቲስት እምነት እነበብሁ፣ የተሳሳቱት የት እንደሆነ የተረዳሁትን እጽፍላት ነበር፤ ለአመት ያህል ከተጻጻፍን በኋላ በይ እንግዲህ በየፊናችን እንጸለይበት፥ እናስብና ከሰድስት ወር በኋላ እንወሰን፤ ውሳኔያችንን በደብዳቤ እናሣውቅ አልኳት። ደብዳቤዋ ምን ምላሽ ይዞ ይመጣ ይሆን ከሚል ስጋት ጋር መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡

***

አንድ ቀን ምሳ እየበላን እያለ ስልክ ተደወለ። ለእናንት ለኢትዮጵያውያን ነው ስለ ተባለ እኔ መላሽ ሆንሁ። የተደወለው ካንድ ቤተ ክርስቲያን ነበር። ከመሃከላችን አንድ ሰው ሄዶ ለአንድ ቡድን ስለኢትጵያ ንግግር እንዲያደርግ ነበር ግብዣው። "ስለ ኢትዮጵያ ምን ምን ለማወቅ ትፈልጋላችሁ? ስላቸው፤ "ስለ ህዝባችሁ፣ ስለ ባህላችሁ፣ ባገራችሁ ስንት ቤት ክርስቲያን (denomination) . . . ወዘተ ንገሩን" አሉ።

ለጓደኞቼ ከነገርኳቸው በኋላ "ስለዚህ ማን እንደምንልክ እንምረጥ" አልኳቸው። "እዚህም እዚያም እየሄድህ የምትዘላብድ አንተው ነህ ስለዚህ አንተው ራስህ ሂድ" አሉኝ። "እንግዲያውስ የምለውን አዘጋጅቼ እመጣና ትጨምሩበታላችሁ" አልኳቸውና ተለየያን። ምን ምን እንደምጠቅስ ጽፌ መጣሁና በጥያቄና መልስ ጊዜ የሚረዳኝ ሰው መድቡልኝ አልኳቸው። በኢትዮጵያ ምን ምን ቤተ ክርስቲያኖች አሉ ለሚለው ጥያቄ ምንም እንኳን ከኦርቶዶክስ ሌላ ቤተክርስቲያን ሌላ የሰም እንድል የፈለጉ ቢሆንም "ያንተን እንዳለ ተናገር" በማለት ተስማሙ፡ "እኔ ልዋሽ አልችልም ሌላ ሰው ይመረጥ" አልኩ፤ በዚህ ሃሳብ ተከፋፈልን። እኔን እንደ እለዳቢም የቆጠሩኝም ነበሩ። ሆኖም ሊናገር የፈለገ ባለመኖሩ እኔው ተወከዬ ከበከሬ አብዱላሄ ጋር ሄድን። የተዘጋጀንበትን አቀረብን፡፡

## ዌስተርን ሚሺጋን ዩኒቨርሲቲ

በመስከረም ለሁላችንም የተሻለ ትምህርት ቤት ተፈልጎልን ተበታተንን፤ እኔና እሰፋ ገብረጊያርጊስ ካላማዙ (Kalamazoo, Michigan) የሚገኘው ዌስተርን ሚሺገን ዩኒቨርሲቲ ተመደብን፡፡ በባቡር ነበር የተጓዝነው፡፡ አብሮን ለሚጓዝ ሰው ከኢትዮጵያ እንደመጣን ስንነግረው "ከኢትዮጵያ የመጣ በፈሎ(Bufflew) ከተማ የሚኖር ሰው አውቃለሁ" ስላለን በፈሎ ከተማ ስንደርስ ባቡሩ ቆም ስላለ ለዛ ሰው ደወልን፡፡ በድምጻቸው ሽማግሌ መሆናቸውን ተረዳን፤ "ወደዚህ አገር መቼ? እንዴት መጡ?" ስንጠይቃቸው፤ እንደሌሎቹ ጥቁሮች እንደመጡ ነገሩን፤ ለካ ከእኛም አገር የመጣ በዚያን ዘመን ነበረ በማለት ተገረመን።

ካላማዙ ከተማ የሜኖናይት ቤተክርስቲያን ስላልነበረ ቅርቤ ባትል ክሪክና ሞርፓርክ ነበር፤ ወደ እዚያም እወሰድ ነበር። በተጨማሪም በባትል ክሪክ ጆን ሰንይደር እና መርል ብራዘርስ የሚባሉት ቤተሰብ ት/ቤት ሲዘጋ እነርሱ ጋር እንዳርፍ አድርገዋል። እልሸን ለመርስ ከሚባል ወጣት ጋር ወደ ሞርፓርክ እንሄድ ነበር፡፡ ፓስተራችን ኤትሮል ላይንቦክ ይባል ነበር፤ ሚስቱ አርማ ምሳ ሳትበሉ አትሄዱም እያለች ወደ ቤታቸው ይወስዱን ነበር።

በዌስተርን ሚሺጋን ለሶስት ሰሜስተር ያህል ነበር የቆየሁት፡፡ የዩኒቨርሲቲ

ትምህርት ጊዜዬን ወደ ኋላ ስመለከት እነኚያ ሶስት ሰሚስተሮች ወሳኝ እንደነበሩ አስባለሁ፡፡ የዶርም ህይወት፣ ከተማሪዎች ጋር የሚደረግ የአመለካከት ግብግብ፣ በተማሪዎች ማህበር በመሳተፍ የሚገኝ ጥቅምና ጉዳት ይህን ሁሉ ያየሁት በዚያን ዘመን ነበር።

በተማሪዎች ማህበር ውስጥ የተሳተፍኩት በኢንተር ቫርሲቲ (INTERVARSITY CHRISTIAN FELOWSHIP (I.V.C.F.) ነበር። በጣም ጠቅሞኛል፤ በየማክሰኞ ማታ ለአንድ ሰዓት ፕሮግራም አላቸው፣ ለኮሌጅ ተማሪ የሚጠቅሙ መልእክቶች ይሰጣሉ፣ አልፎ አልፎ አጫጭር የእረፍት ጊዜ ሲኖር በካምፕ የሚዘጋጁ ኮንፍረንሶች አሉዋቸው፡፡ ከእነዚህ ኮንፍራንሶች ባንዱ ስለ ጥሞና ጊዜ የተሰጠ ትምህርት አሁን አስታውሰዋለሁ። በግሌ በጠዋት ተነስቼ መጽሐፍ የማንበብና መጸለይ ልምድ የጀመርኩት ገና ከመጀመሪያው ነው፤ እኔና ፀጋ ናዝሬትን ለቀን ስንወጣ እንዲህ እንድናደርግ ሚስተር ዌንገር መክረውን ስለነበር፤ ተግባረዕድ ሆኜ በጠዋት ተነስቼ ባናዬን ተከናንቤ መጽሐፍ ቅዱስን አነብ ነበር። እዚህ አሜሪካ መጥቼም ቀጥየበታለሁ። በዚህ በታ ስለጥሞና ያገኘሁት ትምህርት ግን የነበረኝን ልምምድ ይበልጥ ያጠናከረና በሕይወቴ ትልቅ ስፍራ የምሰጠው ነው፡፡

ኢንተርቫርሲቲ የጸሎት ጓድ መርጠን በተወሰነ ጊዜ ተገናኝተን አብረን እንድንጸልይ፣ የሚገጥመንን ችግር እንድንከፋፈል ያበረታቱን ነበር። የጸሎት ጓደኛዬ ማሪየን እንደርሶን ይባል ነበር፡፡ የጸሎት ርዕስ ተለዋውጠን አብረን እንጸልያለን፡፡ አንድ የሳምንት መጨረሻ ወደ ቤቱና ቤተክርስቲያኑ ወስዶኝ ነበር።

እንዲህ ባለሁኔታ የክርስትና ህይወቴ እያደገ፣ የአሜሪካን ኑሮ እየለመድኩት፣ በምማረው ትምህርት እየተለወጥሁ መጣሁ፡፡ ስድስት ወሩን ጠብቆ የፍቅረኛዬ ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ ይህ የእኔና የእርሷን የወደፊት ግንኙነት ወሳኝ የሆነ ደብዳቤ





በጉጉት ከፍቼ አነበብኩት፡፡ በፃፍኩላት ደብዳቤዬ ላይ ምን ወለንሽ ብዬ ለጠየኳት ጥያቄ I AM STILL THERE ብላ መለሰችልኝ፤ የጻፈቺው በትልልቁ ስለነበር፣ ጮክ ብላ እንዳለች ተለማኝና እኔም በልቤ STAY THERE ብዬ ከሃሳቤ አውጥቼ ጣልኳት፡፡ እንደ ድሮዬ ደብዳቢዋ በደረሰኝ በአንድ ሳምንት ዉስጥ መልስ አልሰጠኋትም፡፡ ከአንድ ወር በላይ ቆይቼ መልስ ጻፍኩላት፤ እንዲህ ብዬ፤ 'አንድ ወጣት የሚያገባውን ሲመርጥ መመልከት ያለበት ሦስት ነገሮች ናቸው፤ እነርሱም፣ እምነት፣ መልክ፣ እና ጠባይ ናቸው፤ እምነት ዋና ነው። ምክንያቶቹን ሁሉ እንደገና መዘርዘር አያስፈልግም፤ እንግዲህ እኔ እና አንቺ በዚህ ካልተስማማን ልንጋባ ስለማንችል ግንኙነታችን እዚሁ ላይ ይቁም" አልኳት። ከዚያ በኋላ አልጻፈችልኝም፡፡

ያለሁበት የመንፈሳዊና የአእምሮ ብስለት ይህን ዜና በአወንታዊ መልኩ እንዳስተናግደው ረዳኝ፡፡ የእግዚብሔር ፈቃድ ባይሆን ነው፤ እግዚአብሔር ለእኔ ሌላ እቅድ አለው በማለት በቀለምና መንፈሳዊ ትምህርቴ የማደግ ጥረቴ ላይ ሙሉ በሙሉ አተኮርኩ፡፡

በ1956 ዓም ለመላው አሜሪካና ካናዳ ኢንተርቫርሲቲ ተሳታፊዎች በሶስት አመት አንዴ በካንፔይን ከተማ የኢሊኖይስ ዩኒቨርሲቲ የሚዘጋጀው የሚሽነሪ ኮንፍረንስ ላይ ተገኝቼ ነበር፡፡ እዚያ በየነ ሙላቱን፣ ሙላቱ ባፉን እና ገነት አዋሎምን አገኘሁ፤ በእኔ ካሜራ ፎተግራፍ አብረን ተነሳን፤ የተነሳነውን ፎቶግራፍ ለእያንዳንዳቸው ላኩላቸው። ሙላቱ ባፋ የእርሱን ኮፒ ለሚስቱ ላከላት፤ በጀርባው ማንማን እንደነበርን ጽፎ ነበር። ደስ የሚል ህበረት አደረግን።

በዛ ታላቅ ኮንቬንሽን ላይ የግል ሕይወቴን ምስክርነት እንድሰጥ ስለ ተመረጥኹ መድረክ ላይ ከቢሊግርሃም ጋር አብሬ የመቀመጥ እድል አግኝቼ ነበር። ከእርሳቸው ጋር በአንድ መድረክ ላይ መቀመጥ ለእኔ ትልቅ ክብር ነበር። በዚያ ኮንፍረንስ ላይ አንድ ማታ ከጃፓን የመጣ ተናጋሪ ነበር፡፡ መልእክቱ ብዙዎቻችንን የነካ ለሚስዮናዊነት የሚቀሰቅስ ነበር፡፡ በመልእክቱ መጨረሻ፡ ጸጥ ብለን እንጸልይ አለ። ለጥቂት ደቂቃዎች ከጸለይን በኋላ "ጌታ ወደ ዉጭ አገር እንድትሄዱ

ያሳሰባችሁ እጃችሁን አውጡ" አለን፤ እጄን አወጣሁ፡፡ ቀጥሎም፡- "እናንተ እጅ ያወጣችሁት በአላችሁበት ፀልዩና ወደ መድረኩ ኑ" አለ፡፡ ያላወጣችሁት ድምጽ ሳታሰሙ ወደ የዶርማችሁ ሂዱና ጸልዩ አለን፡፡ እኔ የምሄደው ወደ ዉጭ አገር ሳይሆን ወደ አገሬ ስለሆን ከሌሎች ጋር ወደፊት አልሄድሁም።እየወጣሁ እያለ የቀሩትን ተመለከትሁ፤ ድፍት ብለው ይጸልያሉ፤ ልቤ ይበልጥ ተነካ፤ መኝታ ቤቴ ሄጄ ድፍት ብዬ አለቀስሁ፤ በጌታ ፊትም የምለውን አጣሁ።

## ኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ

ከኢትዮጵያ የመጣነው ለሁለት አመት ለኮላርሺፕ ስለ ሆነ ካላማዙ አንድ አመት ተኩል እንደ ቆየሁ የተሰጠኝ የቆይታ ጊዜ ተጠናቀቀ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሴ በፊት አጭር የመጽሐፍ ቅዱስ ኮርስ ለመውሰድ ስለ ፈለግኹ ኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ (አሁን ዩኒቨርስቲ) አመለከትኩ፡፡ እድሉን አግኝቼ ከጥር እስከ ነሐሴ በኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮርሶች ወሰድሁ። በአብዛኛው የተማርኩት የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ነበር፡፡ ከአለማዊው ዩኒቨርስቲ ወደ ኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ መሄዴን በጣም ወድጄው ነበር፡፡ ብዙ ተማሪዎች በኮሌጁ የተለያዩ ደንቦችና ስርዓቶች፣ ጥብቅነት ቅር ሲሉኝ እኔ በኮሌጁ ደስተኛ ነበርኩ፡፡

ከምናገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ዉጪ ልዩ ጸሎት ቦታና ጊዜ ነበረን፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ብዙዎቹ ሚሲዮናውያን የተማሩበት ኮሌጅ በመሆኑ የበለጠ እንድወደው አደረገኝ፡፡ ወደ ኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ የመጣሁት የሚሲዮኑ ቦርድ ከፍሎልኝ ነው። እዚያም በነበርኩበት ጊዜ ወደ ላንካስተር እየወሰዱኝ ምስክርነቴን እንድሰጥ ያደርጉ ነበር፡፡ ይህም ከትትላቸውንና ፍቅራቸውን እንዳይ ከማድረጉም በላይ በክርስትና ህይወቴ እንዳድግ በጣም ጠቅሞኛል።





***

በአሜሪካን አገር የዩኒቨርስቲ ቆይታዬ ከልጃገረዶች ጓደኞቼ ጋር ወጥቼ ተጫውቼና ሻይ ቡና ተገባብዤ አላውቅም፡፡ በአጋጣሚ የወቅቱን ዝነኛ ዘፋኝ ሃሪ ቦሎፎንቴንን ስለምመስል የእሱን ዘፈን የሚወዱ ልጃገረዶች ባብዛኛው ይገሩቸው እንድወጣና እንድጋብዛቸው ይፈልጉ ነበር፡፡ ጥያቄያቸውን ተቀብዬ አላውቅም ነበር፡፡ ወደ ኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ ስመጣ ጓደኞቼ "ለምን ከሴቶች ጋር አብረህ አትወጣም? ለምን አትጋብዛቸውም?" በማለት መጠየቅ ጀመሩ፡፡ እኔም ፍርጥም ብዬ "እንዴት ከማላገባት ልጃገረድ ጋር እገባበዛለሁ?!" በማለት በእኔ ቤት አፍ የሚያዘጋ መልስ እሰጥ ነበር፡፡ በመልሳቸው ሞገቱኝ "ተሳስተሃል! ከልጃገረዶች ጋር የምትገባበዘው እኮ ስለ ምታገባቸው ብቻ አይደለም፡፡ ለመጨዋወትም ጭምር ነው፤ በአግረ መንገድም ሴቶች ያላቸውን አስተአለሳብ ለማወቅ ይጠቅምሃል" እያሉ ስለ ነዘነዙኝ እኔም አንድ እርብ ማታ ከአንዲት ልጅ ጋር ወደ ቻፕል ልሄድ ተቀጣጠርኩ፡፡ ከልጅቷ ጋር ወደ ቻፕል ሄደን ጎንዋ ተቀምጬ ዲስኩር ሰማን፡፡ ከዚያም ወደ ተማሪዎች ማዕከል ሄደን ለሰላሳ መጠጥና ኬክ በልተን፣ ዳማ ተጫውተን ማደሪያዋ አድርሼያት ወደ ዶርሚቶሪዬ ተመለስሁ፡፡ ወደ ዶርሚቶሪዬ ስደርስ ላውንጅ የነበሩት ጓደኞቼ ያወሩት የነበረው ስለ እኔ ስለ ነበር ሲያዩኝ ሆ! ብለው ከበቡኝ፡፡

ከፍሌ ስገባ ከፍሌን ገለባብጠዋት አገኘሁ፡፡ እኔ ትጭጭት ድረስ እንድማልደርስ ስለሚያውቁ ምረውኛል። እርስ በእርሳቸው የሚደራረጉት አለ፤ አንዱ ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ለብዙ ጊዜ ተጨዋውቶ ለመጋባት መወሰናቸውን ባስታወቀ ቀን መታጠቢያ ቤት ወስደው ከነልብሱ ሻወር ይነከሩታል። እኔ ግን እዚያ እንደማልድረስ ስለሚያውቁ ከፍሌን በመገለባበጥ ብቻ አለፉኝ።

አሜሪካ ከመጣሁ በኋላ ካከናወንኳቸው ነገሮች አንዱ የትርጉም ስራ ነው። THE MENNONITE HOUR የሚባል የራዲዮ ፕሮግራም ሳዳምጥ በመላላክ የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮርስ እንዳላቸው ተረዳሁ፡፡ ጻፍኩላቸውና ላኩልኝ፤ በጣም ቀላልና ግልጽ ኮርስ ነበር። ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምረውን 8ኛውን

ትምህርት በማጥናት ላይ እያለሁ ይህን ጥናት የአገሬ ክርስቲያኖች እንዲያገኙ ተመኘሁ፡፡ ያን ኮርስ ወደ አማርኛ ልተረጉም ወሰንሁና አስፈቅጄአቸው ተረጎምኩት። ትርጉሙን ስጨርስ ቤተክርስቲያኔ እሣትማ ለማስልጠኛ እንድትጠቀምበት ወደ ኢትዮጵያ ላክሁት፡፡ ታትሞ በጥቅም ላይ ዉሎአል። ይህ የትርጉም ስራ የጠቀመው እኔን ነው፡፡

አሜሪካ ስኖር ሜኖናይቶች በየቤታቸውና ቤተ ክርስቲያናቸው እየሄድሁ ከነርሱ ጋር ህብረት እንዲኖረኝ ማድረጋቸው በጣም ረድቶኛል። በእረፍት ጊዜ ከነርሱ ጋር እንዳሳልፍ አድርገዋል። በአቅራቢያዬ ቤተከርስቲያን ሳይኖር ሲቀር አጓጉዘውኛል፡፡ ስተረጉም ረድተውኛል። ስላንካስተርና የኢንዲያና/ሚሺገን ኮንፈረንስና ለሁሉም ሜኖናይቶች ምስጋናዬ ትልቅ ነው።

## ወደ ኢትዮጵያ መመለስ

በነሐሴ ወር 1958 ዓ ም የአሜሪካን ቆይታዬን ጨርሼ ወደ አገሬ ተመለስኩ። ለአይሮፕላን ተጨማሪ ስለማያስከፍል አውሮፓን ለመጎብኘት ወስኜ ጉዞ ጀመርሁ። መጀመርያ የምጎበኘው ሎንዶንን ነበር ፤ ስጉብኝቱ ሁለት ቀን መድቤያለሁ፤ አትላንቲከን ለማቋርጥ የሚፈጀው 8 ሰአት ተኩል ስለነበር ሰው ሁሉ ተኛ። እኔ ግን ወደ አገሬ የመመለሴ ደስታ እንቅልፍ ነስቶኝ አልተኛሁም። ለንደን እንዳረፍኩ ወደ ሜኖናይት የተማሪዎች መኖሪያ ሄጄ እቃዬን አሳርፌ ጉብኝት ጀመርሁ፡፡ በሎንዶን በጣም ያስገርመኝ ባለፎቁ አውቶቡስ ነበር። ከሎንዶን ጉብኝት በኋላ የዓለም ትአይንት (WORLD FAIR) በመታየት ላይ ወዳለበት ወደ ብራስልስ ሄድሁ፡፡

ከዚያ በህዋላ ወደ ፍራንክፎርት ቀጥሎም ወደ ፓሪስ ከዚያም ወደ ሮም ሄድሁ። ከሮም በኋላ ለሶስት ቀን ጉብኝት ወደ ካይሮ በረርሁ። ካይሮ ፒራሚዱን፣ ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን ይዘው በስደት ዘመናቸው አርፈውበት የነበረውንና ሌሎችንም ቦታዎች አይቼ ወደ አዲስ አበባ ለመብረር ወደ አይሮፕላን ማረፊያ





ተጓዝሁ፡፡ ለመሳፈር ትራንሲት ላውንጅ አንድ ሰአት ከቆየን በኋላ በድምጽ ማጉያው Ethiopian Airlines has arrived የሚል ድምጽ ስሰማ ልቤ በደስታ ተሞላች፤ የሃገሬን ስም በድምጽ ማጉያ ስሠማ ለመጀመሪያዬ ነበር።

ጉዞው የሌሊት ስለሆነ ሁሉ ሰው ተኛ፤ እኔ ግን ከአይሮፕላን ስወርድ አሸብርንና ሌሎች ጓደኞቼን ላይ እንደሆን ሳስብ አይኔ አልከደን አለኝ፡፡ አዲስ አበባ ስገባ አሸብር፣ በየነ ጭሜአይበሉ፣ እንግዳ እስፋው፣ ኃይሴ ወልደሚካኤል፣ ንጉሴ አየለ፣ ከፈረንጆችም ሚስተር ሴንሰኒንግ ተቀበሉኝ፡፡ ለሁስት አመት ተኩል የተለየኋቸውን ወገኖቼን አገኘሁ፡፡ ስዚያን ዘመን ውጭ አገር ተልኮ ተምሮ የተመለሰ ሰው በትምህርት ሚኒስቴር ሂሳብ የሚያርፈው እቴጌ ሆቴል ነበር፤ እኔ ግን ከወንድሞቼ ጋር ቀድሞ ወደ ነበርኩበት መርሐ እውራን ት/ቤት ሄድኩ።

***

ነሐሴ 15 ቀን 1958 ዓ.ም አዲስ አበባ እንድገባሁ ያቀድኩት ሜኖኒይት ሚሲዮን ስኮላርሺፕ ስጥቶት ወደ አሜሪካ ስሚሄደው እንግዳ እስፋው ኢትዮጵያን ከመልቀቁ በፊት ገጠመኞቼን መሠረት በማድረግ ለእርሱ ስለ አሜሪካ ነገር ጥቂት ምክር ስመስጠት ነበር። የሚበርበት ቀን ነሐሴ 17 ቀን 1958 ዓ.ም ነበር። እኔ በገባሁ በማግሥቱ ማታ ለእኔ መቀበያ ለእርሱ መሸኛ ዝግጅት ተደርጎ ነበር። በዚያ ፓርቲ ላይ እንግዳ ያለውን አልረሳውም። በእንግሊዝኛ እንዲህ ነበር ያለው፡-

"Only one life that will soon be past, what is done for Christ will last"

ስእንግዳ ሚሲዮኑ ስኮላርሺፕ የሰጠው ተመልሶ ሕዝቡንና አገሩን እንዲያገለግል ነበር፡፡ ስለሆነም ከEastern Mennonite College (EMC) የመጀመሪያ ዲግሪውን እንዳገኘ ተመልሶ ባይብል አካዳሚ ለአንድ አመት አስተማረ፡፡ ከዚያም ወደ አሜሪካ ተመልሶ ሜዲካል ኮሌጅ ገብቶ በሐኪምነት (ዶክተርነት) ተመረቀ፡፡

የቅርብ ጓደኛዬ እንደ መሆኑ "አትመለስም እንዴ?" ስለው "ስፔሻላይዝ ማድረግ አለብኝ" ይለኝ ነበር፡፡ እንዳለውም ቀዶ ጠጋኝ ሆነ፡፡ "ሰው እዚህ በትቅማትና በመሳሰሉት እየተሰቃየ ነው አሁንስ አትመለስም?" እያልሁ ስወተዉተው፡ "አሁንም በአንድ ነገር ስፔሻሊዝ ማድረግ አለብኝ" ብሎ የልብ ቀዶ ጠጋኝ ለመሆን ትምህርት ቀጠለ፡፡ ሊጨርስ አንድ አመት ሲቀረው ሥራ ፍለጋ በ1965 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጣ፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ልዩ ልዩ ሆስፒታሎች በመሄድ እንደ ዶክተር አሥራት ያሉትን አነጋገረ፡፡ በመጨረሻ በቀ. ኃ. ሥ. በጎ አድራጎት ሆስፒታሎች ለማገልገል ወሰነ፡፡ በዚያን ጊዜ የእነዚህ ሆስፒታሎች የበላይ የነበሩትን አቶ አበበ ክበደን እስተዋዉቄው ስለ ነበር እርሳቸውን አነጋግሮ ከድርጅቱ የሰው ኃይል አስተዳደር ጋር ለመነጋገር ሄደ፡፡ የሰው ኃይል አስተዳዳሪዋ ደሞዙን ለመወሰን "አሁን ስንት ያገኛሉ?" ብላ ጠየቀቺው፡፡ "ያ ምን ያስፈልጋል፤ እናንት የምትከፍሉኝን እቀበላለሁ" ሲላት፡ "አይ ልንጎዳዎ አንፈልግም" አለችው፡፡ "እንግዲህ ለማወቅ ከፈለጉ አሁን ተማሪ ነኝ፤ ቢሆንም የሚሰጠኝ በአመት 40,000 ዶላር ነው" አላት፡፡ "ታዲያ ለምን መምጣት ፈለጉ?" ስትለው "እኔ ልመጣ የፈልግሁት የአገሬን ሕዝብ ለመርዳት ፍላጎት ስላለኝ ነው" አላትና በዚያን ጊዜ ያላቸው ትልቁን ስኬል "በወር ብር 1,500 እንከፍሎታልን ብላው ተለያዩ፡፡ ያረፈው እኛ ጋር ስለነበር ማታ ሲመጣ ነው ይህን ሁሉ የነገረኝ፡፡ ሲመለስ ቤት የሚሰራበት 1000 ካሬ ሜትር ቦታ ገዛና የሞርጌጅ ባንክ ሂሳብ ከፍቶ እኔን ወክሎ ተመለሰ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ እየተዘጋጀ እያለ ደርግ ሥልጣን ላይ ወጣ፡፡ ደርግ በተማሩ ሁሉ ላይ ትችት ጀመረ፤ እንግዳም ወደ አገሩ የመመለሱን ነገር ተወው፡፡ የእንግዳ ኢትዮጵያን የማገልገል ነገር ተዳፍኖ አልቀረም፤ አሁን አንድ ድርጅት አቋቋም፣ ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ስፔሻሊስቶችን በማሰባሰብ በአመት አንዴ እየመጣ ለ15 ቀናት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና አዋሳ ልዩ ልዩ የቀዶ ጥገና አገልግሎት እንዲሰጡ እያደረገ ነው፡፡

***





# ምዕራፍ 5

# ከትምህርት መልስ፡- ሥራ፣ ኑሮና ትዳር

## የሻሸመኔ ጉዞ ያተረፈልኝ ቁም ነገር

እንግዳ አስፋው (አሁን ዶ/ር) ከተሸኘ በኋላ እኔን ለመቀበል የተሰበሰቡት ጓደኞቼ ወደ መጡበት ሲመለሱ በየነ ጭሜአይበሉ ለአገልግሎት ወደ ሻሸመኔ ለመሄድ ሲዘጋጅ አብረን እንድንሄድ ጋበዘኝ፡፡ ያኔ ስለ ሻሸመኔ ከተማና አካባቢ ምንም አላውቅም ነበር፡፡ በየነን ስለ ሚሄድበት አገልግሎት ጠየቅኹት፡፡ "ኤስ. አይ. ኤም. በየአመቱ በክረምት ለመምህራን ልዩ የስልጠና ፕሮግራም አለው፤ በፕሮግራሙ መጨረሻ አጠር ያለ የመንፈሳዊ ፕሮግራም ላይ ተናጋሪ እንድሆን ተጋብዤ ነው" አለኝ፡፡ አብሬው እንድሄድና እንዱን ጊዜ እንድወስድም ጠየቀኝ፡፡ ከብዙ ማንገራገር በኋላ አሽታዬን ስገልጽለት ደስ ተለኘ፡፡

እንግዲህ ከአሜሪካ ኢትዮጵያ የገባሁት ሰኞ ነበር፤ እሮብ ጠዋት እንግዳን ወደ አሜሪካ ሸኘን፤ እርብ ጠዋት ጉዞ ወደ ሻሸመኔ ሆነ፡፡ ሻሸመኔ ከመድረሳችን በፊት ኩዬራ የምትባል መንደር ስንደርስ ከአውቶቡሱ ወረድን፡፡ ኩየራ ላይ የኤስ. አይ. ኤም. ሚስዮን የሥጋ ደዌ ሆስፒታልና የሥልጠና ማዕከልም ነበረው፡፡ ሚስዮኑ በየክረምቱ በየቦታው ባሉት ት/ቤቶቻቸው የሚያስተምሩትን መምህራን እዚህ እያመጡ ስልጠና ይሰጧቸዋል፡፡ በስልጠናው መጀመሪያና መጨረሻ መነቃቂያ መንፈሳዊ ፕሮግራም ያደርጉላቸዋል፤ በየነ የተጋበዘው ለዚህ ነበር፡፡

እንደ ደረስን የሥልጠና አስተባባሪዋ ሚስ ሊሲ "እንኳን ደህና መጣችሁ" በማለት ከተቀበለችን በኋላ ወደ እኔ እዮት አደረገች፡፡ በየነም ፈጠን ብሎ "አገራችሁ ለአስኮላርሺፕ ሂዶ ገና ሰኞ ዕለት የተመለሰ ወንድም ነው" ሲል አስተዋወቀኝ፡፡ "ግሩም፣ ለመሆኑ አሜሪካ በነበርክበት ጊዜ በየነ ሙላቱና ሙላቱ ባፋ ከሚባሉ

ልጆቻችን ጋር ተገናኝተህ ይሆን?" አለቺኝ። ሁለቱ ወንድሞች በኤስ አይ ኤም በኩል ለትምህርት የተላኩ ነበሩ:: "አዎ ኸርባና ኢንተርቫርሲቲ ክርስቲያን ፈሎሺፕ ኮንቬንሽን ላይ አግኝቼአቸዋለሁ፤ አውቃቸዋለሁ" ስላት ተደሰተች። የሙላቱን (በኋላ ዶ/ር) ሚስት ዓለሜንና ልጇን ሚዛንን፣ የበየነን እጮኛ የቻለያንሳሽ አግኝተህ ሰላምታ ልትሰጣቸው ይገባልና ልውሰድህ አለችኝና ወደ እነርሱ ቤት አማረን::

እነርሱን ተዋውቄ ዞር ስል አንዲት ቆንጆ ልጅ ሰሌን አንጥፋ ፀሐይ ለትሞቅ አየሁ ፤ትኩረቴን ሣባችው። እርሷም "ግደይ ትባላለች" በማለት አስተዋወቀችን። ወደ ክፍላችን ስንሄድ ልጅቷን ዞር ብዬ እንደ ገና በትኩረት እንዳየኋት የዶክተር ሙላቱ ባለቤት ወ/ሮ ዓለሜ ታወራለች።

***

በፕሮግራሙ መሐል እኔና በየነ ከግቢው ወጣ ብለን እየተንሸራሸርን እቅደን ስለነበረው ሚሺን ስለ ማቋቋም በጥቂቱ ተነጋገርን:: እኔ ወደ አሜሪካ ከሄድሁ በኋላ በጉዳዩ ብዙ እንዳልተነጋገሩበት ነገረኝ:: "ያንተስ እቅድህ ምንድነው?" በማለት በየነ ጠየቀኝ:: "እንግዲህ የእኔ የመጀመሪያው ሥራዬ ሚስት መፈለግ ነው" እልኩትና አያይዤ፤ "እረ ለመሆኑ ክርስቲያን ልጅ አገኛለሁ?" በማለት ጠየኩት:: "እሱ አይጠፉም፣ ያቺ እዚህ ያየናትስ?" አለኝ በየነ:: ሰሌን ላይ ተቀምጣ ያየኋት ደስ ያለችኝን ልጅ እንዳለ ገባኝ:: "ጌታን የምታውቅ ይመስልሃል?" አልኩት:: "እዚህ እየኖረች ላታውቅ አትቀርም" አለኝ:: መልሱ አላረካኝም:: የበለጠ ለማወቅ ፈለኩ:: ከኩዬራ ከመውጣታችን በፊት እንዴት ይበልጥ እንደምተዋወቃት ዘዴ ፈለግን። በሚቀጥለው መስከረም በናዝሬት እመቤታዊ መንፈሳዊ ኮንፍረንስ እንዲገኙ ስለቱንም እንጋበዛቸው ተባባልን።

አለሜና የቻለያንላሽ ፡ ፍቅረኞቻቸውን ያገኘ ሰው በማየታቸው ተደስተዋል:: ይህንንም ደስታቸውን ለመግለጽ እኔና በየነን ምሳ ቤታቸው ጋበዙን። ግብዣው ግደይን የማገኝበት እድል በመሆኑ እስደሰተኝ:: ሁለቱ በማስተናገዱ ላይ አተኩረው ስለ ነበር ግደይ ከእኛ ጋር እኩል ቀጭ ብላ ተጋበዘች:: ከግደይ





ጋር ማዕድ መቅረባችን የፈጠረብኝ ስሜት ልዩ ነበር:: ሶስቱም በተላከላቸው ፎቶግራፍ ላይ እንዳዩኝ ነግረውኝ ፎተግራፉን አውጥተው አሳዩኝ። ፎተግራፉ ኧርቫና በተገናኘን ጊዜ እኔ ያነሳሁት ነበር:: በጀርባው ስማችን ተገልጿል፤ ሙላቱ፣ በየኔ፣ ገነት አውዓሎም እና ሚሊዮን። ግደይ ሚሊዮን የሚለውን ስም ስታይ እንዴት ደስ የሚል ስም ነው ማለቷን ነገሩን። ደስ አለኝ (በስሜ የተነደፈቺው ያኔ እንደ ሆነ በኋላ ነግራኛለች)::

ምሳ እየበላን "የዚህ አገር ማለት የሻሸመኔ ልጅ ነሽ?" ብዬ ጠየኳት:: "አመሰላለሁ እንዴ?!" (የባላገር ልጅ አድርጌ በመቁጠሬ ቅር እንዳላት በአባባሏ ይነበባል) "የአሥመራ ልጅ ነኝ" አለች:: "ታዲያ እዚህ እንዴት መጣሽ?" አልኳት:: "አባቴ ሻሸመኔ ከተማ ዉስጥ ትልቅ ሆቴል አለው፤ ነርስነት እንድማር እዚህ አስገባኝ" አለችኝ። "ቤተሰባችሁ ከአሥመራ እንዴት ወደ ሻሸመኔ ሊመጡ ቻሉ?" ብዬ ደግሜ ጠየኳት:: ግደይ "ታሪኩ ረዘም ይላል፤ ከአስመራ እንደወጣን አባቴ አዲግራት የጉምሩክ መስሪያ ቤት ይሠራ ነበር፤ ከዚያ ወደ አዲስ አበባ መጣን፤ ራስ ደስታ ሆስፒታል አጠገብ ትንሽ እንደኖርን አባቴ የአሰላ ሆስፒታል አስተዳዳሪ ሆኖ እንዲሰራ ተላከ፤ ትንሽ ከቆየ በኋላ እዚያ ሥራ አቆመ፤ በቃ ወደ እዚህ መጣንና ሻሸመኔ መኖር ጀመርን" በማለት ረዥሙን ታሪክ እሣጥራ ነገረችኝ። "በአሆኑ ሰዓት ምን እየሠራሽ ነው ታዲያ?" አልኳት የንግግር ልውውጣችንን ለማስቀጠል በሚፈልግ ሰሜት::

"የእዋላጅነት ትምህርት ለመጀመር እየተዘጋጀሁ ነው፤ የዚህ ሆስፒታል መስራች ዶክተር ቶምሰን አስተምራታለሁ፥ ስኮላርሺፕም አፈልግላታለሁ ብለው ከአባቴ ጋር እየተነጋገሩ ነው:: እስከዚያው እዚህ ሆኜ የመጀመሪያ ደረጃ ድሬሰርነት ፈተና ወስጄ አልፌአለሁ።" አለችኝ::

ከበየነ ጋር ያቀድነውን የማሣካበት እድል እንዳገኘሁ ስለገባኝ "በነገራችን ላይ ናዝሬት እመቤታዊ መንፈሳዊ ኮንፈረንስ አለ፣ ተካፍለሽ ታውቂያለሽ? ሶስታችሁንም እንጋብዛችሁ" በማለት ጋበዝኳት:: "ተካፍዬ አላውቅም፤ ግን ስለዚያ ኮንፈረንስ ሰምቻለሁ፤ መካፈልም እፈልጋለሁ" አለች:: "ታዲያ ለሚቀጥለው ኮንፈረንስ

ሶስታችሁም ለምን አትመጡም?" ብዬ በግብግቦዬ ገፋሁበት፡፡ ግደይም "የእነርሱን አላውቅም፤ እኔ ግን ለመሳተፍ ፈቃድ እጠይቃለሁ" አለች፡፡ "መልካም ነው፤ እኔና በየነም ለለምንከፈል እዛ እንሄዳለን" አልኳት፡፡

የእርሻናውን ፎቶ እንዳነሳሁት ሁሉ አስሜ ሰባኗ የምትልከው የልጇን ፎቶግራፍ ላንሳልሽ አልኳት፡፡ ለውር አቅዴ የግደይን ፎቶግራፍ ለማንሳት ነበር፡፡ ተሳካልኝ አለሜም ተስማማች። በየነ ከሌሎቹ ጋር እየተጫዋወተ እያለ አንድ ጀሮውን ወደ እኛ ጣል አድርጎ ስለነበር "በል አንግዲህ ፎተግራፉን አንሳና እንሄድ" አለ።



ግደይን ለመጀመሪያ ጊዜ ባየኋት ወቅት ለእነ ዶር ሙላቱ ለመላክ የተነሳነው ፎቶ

በመስከረም ናዝሬት እንገናኝ ተባብለን ተለያየን። የኔና የግደይ ግንኙነት የተጀመረው እንዲህ ነበር፤ ይህን የሻሸመኔ ጉዞ ታላቅ ያደረገውም ከስተት ይህ ነው። የደደሩና የአስመራዩቱ (አዲሃርቦ) ልጆች፣ ከምስራቅና ከሰሜን መጥተን መሐል አገር ተገናኘን። ከበየነ ጋር የመጣንበትን ፕሮግራም በሚገባ አሳክተን ከሁሉም በላይ እኔ እጮኛ አግኝቼ ወደ አዲስ አበባ ተመለስን። ባስታወስኩት ቁጥር "ታላቁ ጉዞ" እለዋለሁ፤ ከጉልምስና እስከ እርጅና አብራኝ ልትዘልቅ የቻለችውን ቆንጆ ያገኘሁበት አጋጣሚ ነውና፡፡

***





## እንደ ገና ሐረርቲ

ከሻሸመኔ መልስ የመጀመሪያ ሥራዬ መምጣቴን ለትምህርት ሚኒስቴር ማስታወቅ ነበር፡፡ ለእስኮላርሺፕ ስንሄድ ጃንሆይ ፊት ቀርበን እንደተሰናበትን ሁሉ ስንመለስም እጅ መንሳት እንዳለብኝ ተነገረኝ። መቼም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ያሳለፍኩት ውጣ ውረድ፤ ጃንሆይ ፊት ለመቅረብ የነበረው መጓተት አይረሳኝም፡፡

ለማንኛውም የቅጥር ደብዳቤየን ከጨበጥሁ በኋላ ዘመዶቼን ለማየት ከአሸብር ጋር ወደ ደደር ከዚያም ወደ ሃሪርቲ አመራን። በዚያን ወቅት ወንድሜ አሸብር የተግባር ዕድ ተማሪ ሲሆን ቴሌ ኮሙኒኬሽን የክረምት ሥራ ይሠራ ነበር። እርሱም ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ቤተሰቡን ለማየት ስለፈለገ፣ ጊዜያዊ ሥራውን አቁሞ ከአዲስ አበባ በማታ ባቡር ተሳፍረን ድሬዳዋ ገባን፡፡ ወደ ደደር ጉዟችንን ቀጠልን። ደደር እንደደረስን አባዬ አስገደች በዚያን ጊዜ ትዳሯ በቋፍ ላይ ቢሆንም ከባልዋ ከጋሼ ግዛው ጋር ስለምትኖር እርሷን ለእፍታ አይተን ጉዞአችንን ወደ ሃሪርቲ ልንቀጥል ተነሣን፡፡

አድራችሁ ነገ አብረን እንሄዳለን ብትለንም እናድርም መሄድ አሰብን ስንላት እርሷም አብራን ወደ ሃሪርቲ ጉዟችንን ቀጠልን፡፡ ሶስታችንም ወደ ማታ ሃሪርቲ ስንደርስ አባዬ ሶስቱን ታላላቅ ልጆችዋን በአንድነት ማየቷ አስፈነደቃት እልልታዋን አቀሰጠችው። ከአሜሪካ ከተመለስሁ በኋላ ኤሌትሪክ በሌለበት ሳመሽ የመጀመሪያ ቀኔ ነበር፡፡ ቢል ቢል የሚለው የኩራዝ መብራት ነበረች ለቤቱ ብርሃን የምትፈጥረው፡፡ የዘመዶቼን ብቻ ሳይሆን የአገሬው በጭለማ መኖር በግልጽ ታየኝ። ጭለማ ዉስጥ ብንሆንም ግን ከቤተሰቤ ጋር የነበረኝ ዉይይት የሞቀ ነበር። የበለጠና አጸደ ልጆች ሁላችንም አብረን ሆነን የተጫጫንበት ያን ቀን ምሽት ነበር፡፡

ምድጃው ላይ የተጣደውን ድስት ለማብሰል የሚነደው እሳት ተጨማሪ ብርሃን ከመስጠቱም ሌላ ለከረምቱ ብርድ ሙቀት ይለግሳል፡፡ ሁሉም በየፊናቸው ስለአሜሪካ ኑሮዬ ጥያቄያቸውን አዥጎደጎዱ።

"ለመሆኑ የምትበሉት ምንድነው? እንጀራ አላቸው?" አለች አባዬ::

"አይ! እንጀራ የላቸውም" - አልኩ::

"እንጀራ ከሌለ ታዲያ ምን ትበላላችሁ?" ቀጠለ አባብዬ:: "ከአትክልት፣ ከልዩ ልዩ እህልና ከሥጋ የሚሠራ ምግብ ነው" በማለት ጨመርሁ::

"ከብቱን ማን ያርድላችኋል?" አለች አባዬ በትዝብት ድምጸት::

"ሁሉ ነገር የሚሠራው በኤሌትሪክ ስለ ሆነ ከብቶችም የሚታረዱት በኤሌትሪክ ነው" አልኩት::

"በስማም! በሰው ተባርኮ ያልታረደ ስለ ሆነ ስትበላ የከረምከው በክት ነው በለኛ! መጥሐፈ ቄደር መጠመቅ አለብህ፤ ለመሆኑ ዓርብና እሮብ ትጦማላችሁ?" አለ እንደ ገና እየዘገነነው::

"እዚያ አገር ዓርብ ሮብ የሚባል ጾም የለም" አልኩት::

"እውነትም ለመምሬ በቀለ ነግረን መጥሐፈ ቄደር መጠመቅ አለብህ" እርግጠኝነት እየተሠማው::

ምርመራው በዚህ ብቻ አላበቃም:: ወንድሜ ከተማም የራሱ ጥያቄዎች ነበሩት - በግንዛቤው ልክ::

"በአውሮፕላን ስትበር ከዛ ላይ እወድቃለሁ ብለህ አትፈራም?" አለ ከተማ:: አይሮፕላን በሰማይ ሲበር ሲያይ ወደ ላይ አንጋጦ ጋሼ ሚሊዮን እዛ ዉስጥ ነው ይል እንደ ነበር ተነግሮኛል:: "አይሮፕላን ዉስጡ እንደ ሰቀላ ቤት ነው፤ በዉስጡ ብዙ ሰዎች አሉ፤ አያስፈራም" በማለት ላስረዳው ሞከርኩ:: ማብራሪያዬ አልገባውም ከተማ "እዚያች ትንሽ ነገር ሰማይ ላይ አምትበር ነገር ዉስጥ እንዴት ብዙ ሰው ይኖራል?" በማለት ደግሞ ጠየቀኝ::

አሸብር "ከቴ አንድ ቀን አንተም እዚያ ላይ ትወጣና ትሄዳለህ" በማለት የጥያቄውን አቅጣጫ አስቀየረልኝ::





"አይ እኔ አልፈልግም፤ እፈራለሁ" አለ ከተማ:: የደረስሁ ዕለት ማታ የነበረው ጭውውቱ ይህን ይመስል ነበር::

ወላጆቼን ከመሄዴ በፊት መጾም እንዳቆምሁ ስላላወቁ አለመፆሜ አሳሰባቸዋል። አባዬ "መጾም መጀመር አለብህ" ብላ እሮብ ጠዋት ስነላ ቁጢ ያለ ወተት ለጠቺኝ፤ እኔ ወደ ማድቤት ሄጄ ወተቴን ጨምሬ እየጠጣሁ ስመጣ አይታ፤ "እይ! እንግዲህ እንደፈለግህ አድርግ" በማለት ተወቺኝ:: በእርሷ ቤት አሸብር ጧሚ ነው፤ ሐሙስ ማታ ቁጭ ብለን ስንጨዋወት "ወንድምህ ተበላሽቶ መጥቷል፤ መጾም አለበት" አለችው:: አሸብርም አስደንጋጭ መልስ ሰጣት "እንዲህ ያለውን ጦም የደነገጉት ቄሶች ናቸው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ የለም" አላት:: አባዬ ደንግጣ "እንዴት በመጣፉ የለም?" በማለት ጠየቀች:: አሸብር አቋሙን በመግለጥ የበለጠ አስደነገጣት: "ጥምቀት ወይም የገና በዓል እሮብ ቢውል ጋድ ነው ይባልና እሮብ አይጦምም፤ የሚጠመው ማከሰኞ ነው፤ ቄሶች እንዲህ ያደረጉት ጥሩ ምግብ ሕዝበ ክርስቲያን እንዲያመጣላቸው ለማድረግ ነው፤ ስለዚህ እሮብና ዓርብ መጦም አያስፈልግም" አላት ፍርጥም ብሎ:: አባዬ ተስፋ በቆረጠ ድምጽ "እዬ ጉድ ለካ አንተም እዚሁ ሆነህ ትበላሽተሃል፤ እንደፈሊጋችሁ!" አለች።

ያቺ ምሽት ለእኔ ልዩ ነበረች፤ ሁሉም የበለጠ ልጆች አብረን ያመሸንባት የመጀመሪያ ቀንም ነበረች:: እከሊል፥ቤቴልና ማርታ እኔ ለትምህርት ወደ ሸዋ ከመጣሁ በኋላ ነው የተወለዱት። የመጨረሻችን እንደምትሆን ግን አንዳችንም አልጠረጠርንም:: አባዬ አስገደች የመጀመሪያ ልጇን ሲሻንን ከእባቷ ጋር ደደር ትታ መጥታለች:: ሁላችንም አብረን በመሆናችን ፎቶግራፍ መነሳት አለብን ብዬ ከኋላችን የሚሆን አንሶላ አጥር ላይ ሰቅዬ፣ ካሜራው ራሱ እንዲያነሳን አደራጅቼ (self timer) እራሴ ታሪካዊ ፎቶግራፍ አነሳሁ::



*የበለጠ ወ/ገብርኄልና እፀደ ወ/ሰንበት ቤተሰብ*

ዓርብ ጠዋት እባዬ የአንቁላል ፍርፍር ስርታ ቁጢ በወተት አድርጋ ለእኔና ለአሸብር ሰጠቺን። እባታችን በዚህ ድርጊቷ ተገረመ፤ "እንዴት እንዲህ ታደርጊያለሽ" ብሎ እናታችንን አንደመቆጣት አለ:: "እኔ እዚህ ባልሰጣቸው ሲመለሱ መብላታቸው ይቀራል?" አለቺው። እባታችን እኔን መጥሐፊ ቄደር ሊያስጥምቀኝ የነበረውን ሃሳብም ተወው።

የሃሪርቲውን ጉብኝታችንን ከፈጸምን በኋላ ሚኖ ያሉትን አጎቶቻችንን እየን። እኔ ሚኖ ያሉትን የቆሎ ጓደኞቼን ለማየት ብፈልግም አልቻልሁም:: የት እንዳሉም ማወቅ አልተቻለም። እኔና አሸብር ጉዞአችንን ወደ ደደር ቀጠልን፤ አባዬ አስገደች ቀደም ብላ ወደ ቤትዋ ተመልሳ የእኛን መምጣት ትጠባበቃለች። አሰጌ ምን ምግብ እንደምታዘጋጅ ሳይቸገራት አልቀረም፤ ቢሆንም ሩዝ ቀቅላ ከፉርኖ ዳቦ ጋር አቀረበችልንና ምሳ በላን።

ከደደር ጉብኝት በኋላ የአክስታችተን ልጅ እበራሽን ለመጎብኘት ወደ ሙጢ ሄድን። ከሁለት አመት በፊት የሞተው የወንድሟን ፍሥሐን አርም አወጣሁ፥ ሃዘኔን ገለጽኩ:: በፍስሃ ሞት እጅግ አዝኜ ነበር:: ከአንድ ሆድ እንውጣ እንጂ ለእኔና አሸብር ልክ እንደ ወንድማችን ነበር:: የፍስሃ ሞት አስከዛሬ ድረስ ያሳዝነኛል ሃዘኑ አለቀቀኝም::





## አሸብርና ፍስሐ

እኔ በ1944 ዓ ም መጨረሻ የሁለተኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና ከወሰድኩ በኋላ ፈተናው ወደ ደደር አልመጣም:: አሸብር የሁለተኛ ደረጃ ፈተናውን ለመፈተን ብዙ ጥረት አድርጓል:: ተሳኩቶለት የተፈተነው በ1947 ዓ ም መጨረሻ ነው:: አሸብር ደደር ሆኖ መፈተን እንደማይችል ካወቀ በኋላ ሌሎች እንዳደረጉት ወደ ድሬዳዋ መጥቶ ለመፈተን ወሰነ:: በድሬዳዋ ያለን የቅርብ ዘመድ የእናታችን አጎት ጋሽ ዘገዬ ነበር:: ከእናታችን ጋር ተመካከሮ አንድ ኩንታል ያህል ማሽላ ይዞ ወደ ድሬዳዋ መጥቶ ጋሼ ዘገዬና ሚስቱ ጋር ተጠጋ። ክርስቶስ ት/ቤት የ8ኛ ክፍል ትምህርቱን መማር ቀጠለ:: ትምህርቱን ጠንክሮ ለማጥናትና ውጭ ላለማምሸት ወሰነ:: ይህን ውሳኔውን እንዲያጠናክርለት ከወላጆቻችን እንደ ተጻፈ አድርጎ ለጋሽ ዘገዬ ደብዳቤ ጻፈ:: አንድ ሰውዬ ትምህርት ቤት ድረስ መጥቶ ይህን ደብዳቤ ሰጠኝ ብሎ በፖስታ አሽጎ ለጋሼ ዘገዬ ሰጠው።

"ይድረስ ለአቶ ዘገዬ ወልደአማኑኤልና ወ/ሮ አዛለች፤ የሰማይ ረቂቱን፣ የምድር ሰፋቱን ያህል እንደምን አላችሁ? እኛ ከእናንተ ናፍቆት በስተቀር መድኃኔ ዓለም ይመስገን ደህና ነን። ልጃችን አሸብር ወደ እናንተ የመጣው ስለትምህርቱ ተቸግሮ ነው፤ ስለ ችግሩ በሚገባ ሳይነግራችሁ አይቀርም፤ እንደ ወንድሙ መሊሆን ሁለተኛ ደረጃ የሚያስገባውን ፈተና ለመፈተን ብሎ ነው:: በከተማ ኑሮ እንደምትቸገሩ እናውቃለን፤ ቢሆንም አሸብር ለእናንተም ልጃችሁ ነውና ተቸገሩልን:: እርሱም እንዳይበላሽ አደራ፤ ብዙ ጨዋታ እንዳያበዛ ምከሩት፤ ተቆጣጠሩት፤ በተለይ ማታ ከአንድ ሰአት በኋላ ውጭ እንዳይወጣ አደራ፤ ያለእናንተ ፈቃድ ቢያመሽ እስራችሁ ግረፉት። ይላሉ በለጠ ወልደ ገብርኤልና እፀደ ወልደ ሰንበት"::

አንድ ቀን ታዲያ በት/ቤታቸው ትያትር ለማሳየት ልምምድ ሲያደርጉ አምሽቶ ቤት ገባ:: ጋሽ ዘገዬም በደብዳቤ ጭምር የተሰጣቸውን አደራ ስመወጣት ተቆጥቶ "ውጭ እንዳታመሽ ብዬህ አልነበረም?" ብሎ ሊገርፈው አርጩሜውን ሊያነሳ ሲል አሸብር በመርበትበት "የቆየሁት ት/ቤት የቲያትር ልምምድ ሳደርግ

ነው፤ ነገ ከመምህሬ ወረቀት አመጣለሁ" ብሎ ሳይገረፍ ቀረ።

ድሬዳዋ ቢሆንም ቤት ዉስጥ ኤሌትሪክ ስላልነበራቸው ለማጥናት ይቸገር ነበር። አንደ እድል ሆኖ ግን አንዱ የከተማ ዉስጥ መብራት የተንጠለጠለበት ምሰሶ የተተከለው በራፋቸው ላይ በመሆኑ የቤቱ በር ሲከፈት ብርሃኑ ወደ ቤት ይገባል። ስለዚህ በሩን እየከፈተ በሚገባው ብርሃን እያጠና ፈተናውን በማለፉ እርሱም አዲስ አበባ መጥቶ ተግባረዕድ ት/ቤት ገብቶ በኤሌትሪክ ሙያ ሊመረቅ ቻለ። ከዘመናት በኋላም ድሬድዋ ለጉብኝት ስንሄድ ያቺን አምፖል ወደ ላይ አንጋጦ አያየት "አንጀራዬን ያወጣሽ" በማለት አሞካሽቷታል።

በ1946 ዓ ም አሸብር መጨረሻ ወደ ድሬዳዋ ሲሄድ በ1947 ዓ ም መጨረሻ ፍስሃ ወደ ሐረር ሄደ። ወደዚያ የሄደው አከስታችን አባዬ ዘነበች እዚያ ስለነበረች ነበር። በእርሷ ላይ ጫና ሳለመሆን ብሎ ለአንድ አረብ ተቀጥሮ ቀን ቀን እየተማረ ማታ ማታ ለአረቡ ሸቀጥ እየሸጠ እዚያቺው ባንኮኒ ስር አንጥፎ ያድር ነበር። በ1948 ዓ ም መጨረሻ እርሱም ተፈተነና እልፎ ጂማ እርሻ ት/ቤት አንደተመደበ አሜሪካ ሆኜ ሰማሁ። በጣም ደስ አለኝ።

በ1949 መጨረሻ አሸብር ፍስሐን ይዞ ወደ አዲስ አበባ ሊያመጣው ወደ ሐረር ሄደ። በደረሰ በማግስቱ ወደ አዲስ አበባ ሊሄዱ አቅደው እንደልማዳቸው ተቃቅፈው ተኙ። ጠዋት ፍሥኃ አሞኛል ዛሬ ልንሄድ አንችልም ሰላለ ላይሄዱ ዋሉ፤ በማግሉቱም ጤናው ያው ነበር። በሦስተኛውም ቀን ለላልተሻለው በል አንግዲህ ሲሻለህ ና ብሎ አሸብር ጥሎት ወደ አዲስ አበባ ሄደ። አሸብር አዲስ አበባ ሆኖ ለ15 ቀን ባቡር ጣቢያ እየተመላለስ ይጠብቀው ነበር።

አንድ ቀን አንድ የሐረር ልጅ አየና ቢጠይቀው ፍሰሐ መሞቱን ነገረው። አሸብር መርዶውን ሰምቶ ወደ ት/ቤቱ ተመለሰ። እኔ አሜሪካ ሆኜ ከዛሬ ነገ ጅማ ሰለመድረሱ ደብዳቤ አጠባበቅ ነበር። አሸብር እንዳይነግረኝ ቤተሰብ በጥብቅ አሳስቦታል። ውትወታዬ ስለበዛበት የመርዶ ደብዳቤ ጽፎ ሳከልኝ። ደብዳቤው የደረሰኝ ከምሳ በኋላ ስለነበር ወደ ላውንጅ ሄጄ ፖስታውን ከፍቼ አነበብሁ።





መርዶውን ሰሰማ ተነሳሁና ወዲያ ወዲህ ተንጎራደድሁ፤ ወደ መኝታ ቤቴ ሄጄ ታጋደምሁ። ያን ሉት ከሰአት በኋላ ያለኝ የማሺን ሾፕ ልምምድ ስለነበር የሞት ሞቴን ወደ እዚያ ሄድሁ። የምሰራው እየተበላሸብኝ ለለተቸገርሁ ለጓደኛዬ ለአሰፋ ገ/ጊዮርጊስ የሰማሁትን መርዶ ነግሬው ከአለተማሪዬ ፈቃድ ጠይቄ ወደ መኝታ ቤቴ ልቆዝም ሄድሁ። እንግዲህ ከአሸብር ጋር ሙጢ የሄድነው የዚህ ወንድሜን እርም ላወጣ ነበር።

ከቀናት በኋላ አባዬ የሺን ለማየት ወድ ሙጢ ሄድን። የሞተው ከሁለት አመት በፊት ቢሆንም አባዬ የሺ አልተጽናናችም ነበር። እኔና አሸብርን ስታይ ፍሥኃዬን አምጡ ብላ ጩኸትዋን ለቀቀቺው። አባዬ የሺ ሁልጊዜ ባየቺኝ ቁጥር ፍሥኃን እያስታወሰች ትቆዝማለች፤ እኔም እንዲሁ።

## ተግባረዕድ - በመምህርነት

እንደታቀደው ትምህርት ሚኒስቴር የመደበኝ ተግባረዕድ ት/ቤት ነበር። ዘመዶቼን አይቼ አዲስ አበባ ከተመለለኩ በኋላ ፒያሳ ከሲኒማ አምፒር ወደ ታች ወርዶ አንዲት ሁለት ከፍል ቤት በ35 ብር ተከራየሁ። ከውጭ የወጥ ቤት ቢኖራትም ምግብ የምበላው በየሆቴሉ እየዞርሁ ነበር። በ50 ሳንቲም ምሳዬን ግሩም ቀይና አልጫ ወጥ ሽፍንፍን እበላለሁ (ሽፍንፍን የሚባለው በአሮብና አርብ የፍሰግ ምግብ ለመብላት የሚያፍር ሰው የሚበላው እንዳይታወቅበት የወጣ ሰም ነው)። ማታ ራቴን ጎዊዶ በሚባል የፈረንጅ ምግብ ቤት 1.50 ብር ከፍዬ አበላለሁ።

የእንቁጣጣሽ ማግሰት የአመቱ የሥራ ቀን መጀመሪያ በመሆኑ ወደ ት/ቤት ሄጄ በመጀመሪያው የመምህራን ሰብሰባ በመገኘት ለዲሬክተሩና ለሥራ ጓደኞቼ መምጣቴን አሣወቅኩ። ትምህርት የሚጀምረው ግን መስከረም 18 ነበር። ከናዝሬቱ ኮንፍረንስ ጋር እያይገቼ እነ ግደይን ከቀጠርኩበት ጋር ተገጣጠመልኝ።

ቀኑ ሲደርስ በዚያ ስብሰባ ለመገኘት ወደ ናዝሬት ሄድሁ። ግደይም መጣ።

በአጋጣሚ የመጀመሪያ ፍቅረኛዬም ኮንፍረንሱ ላይ ለመገኘት መጥታ ነበር። አይኔን በግደይ ላይ መጣሌን የሚያውቁ በየነና ንጉሴ አየለ ብቻ ነበሩ። በእዚያ ኮንፈረንስ ላይ ልጃገረዶቹ መዝሙር ያሰሙ ነበር። በሚደንቅ አጋጣሚ ልጅቷና ግደይ ጎን ለጎን ቆመው ነበር የዘመሩት። ንጉሴ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ "በል አንግዲህ ለማወዳደር ከዚህ የተሻለ እድል የለህም" በማለት አንሾካሾከልኝ። ከልጅቷ ጋር ለምን እንዳቆምን ለለማያውቅ የቀልዱን ነበር የተናገረው። በአጭሩ የተለያየነው በአምነት ምክንያት ነበር። እርሷ የአድቬንቲስት እምነት የምትከተል ስለሆነችና ለመለወጥ ፈቃደኛ ባለመሆኗ ነው። አሜሪካ እያለሁ በደብዳቤ ግንኙነታችንን ካቋረጥን በኋላ አዲስ አበባ ቤት ተከራይቼ አንደ ገባሁ ከጓደኛዋ ጋር መጥታ ጎብኝታኛለች፤ የሚገርመኝ ነገር ከዚያ ወዲህ እርሷን አይቼአት አላውቅም።

## የእኔና ግደይ መግባባት ጨመረ


የመጀመሪያ አብሮነት መስከረም 1951 ቆቃ ግድብ

በኮንፈረንሱ ማግሥት ግደይ አህቷ ንግሥቲ ቤት ለምሳ ጋብዛኝ ሄድሁ። ከምሳ በኋላ ለሽርሽር ወደ ቆቃ ሄድን። ቆቃ አንዲት ዛፍ ስር ቁጭ ብለን ያወራንበት

ቦታ አሁን በውኃ ተሸፍኖአል። በማግሥቱ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ስለነበረብኝ፣ ግደይም ወደ አዲስ አበባ ሄዳ ከዚያም ወደ ሻሸመኔ መሄድ ስላለባት በጠዋት ወደ አዲስ አበባ አብረን ተመለስን። መርካቶ አጎቷ ቤት





አድርሼያት ልንለያይ ስንል ከፋን፤ ለአንድ ቀንም ቢሆን መለየየቱን አልፈለግንም። ፈቃድሽ ቢሆን ጎጆዬን ላሳይሽና ነገ ወደ አገርሽ ትሄጂያለሽ አልኳት፤ መልካም ነው ብላ እቃዋን አስቀምጣ ወደ ፒያሳ መጣን። ቤቴ ቁጭ ብለን ሰፋ ያለ ጭውውት ጀመርን።

በትምህርት ጨዋታ ዳርዳሩን ስዞር ቆይቼ በልቤ የሚጉላላውን ጥያቄ አፈረጥኩት። ሁለት ወጣቶች እንዲህ ከተቀራረቡ ግንኙነታቸው ወደ ጋብቻ ማምራቱ አይቀርም፤ ለመሆኑ አንቺ "እጮኛ ወይም ልታጪው ያሰብሺው የለሺምን?" በማለት። "ነበረኝ፤ ጥሩ ሥራም ነበረው፤ ባለ መኪናም ነበር፤ ግን አቋርጠናል" አለችኝ። ማቋረጣቸው በውስጤ ደስታና መረጋጋት እንደ ፈጠረልኝ ሳላውቅ "ለምን አቋረጣችሁ?" በማለት ጠየኳት። መግለጫ ለጠችኝ። "አንተስ?" በማለት የተጠያቂነቱን ተራ ወደ እኔ አዞረችው። "ነበረችኝ፣ ግን ትተናል" አልኳት። "ለምን አቋረጣችሁ?" የራሴኑ ጥያቄ ደገመችልኝ። "በእምነት ምክንያት" በማለት በለፈው አለረዳኋት።

ብዙ ተጨዋወትንና ወደ አጎቷ ቤት እየሄድን እያለ፤ ቅድም እንዳልሁት "እንግዲህ ሁለታችን ይሄን ያህል ከተጨዋወትን ይህ ሂደት ወደ ጋብቻ ያመራ ይሆናል፤ በሚገባ በደንብ ለለማታውቂኝ እኔም ስለማላውቅሽ ፈረንጆች እንደሚሉት አሁን የጋብቻ ጥያቄ ላቀርብልሽ አልችልም። ግን ወደ እዛው ልንጓዝ እንችላለን፤ ስለ ራሴ በመጠኑ ነግሬሻለሁ፤ ዓላማዬንም ልታውቂ ይገባል፤ በአጭሩ አላማዬ ክርስቶስን ማገልገል ነው። ይህ ምን እንደሚያስከትል አላውቅም፤ እንደዚህ ወዳለ ህይወት እንድትገቢ አሁን መጠየቅ ሊከብድ ይችላል። በደበልጥ መተተዋወቅ ይገባናል። ፈቃድሽ ከሆነ በዚህ መንፈስ ጓደኝነታችንን ልንቀጥል እንችላለን፤ እንድንቀጥል ትፈቅጃለሽ?ን" አልኳት። "የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ደስ ይለኛል" አለችና ወደ አጎቷ ቤት መሄዱን ቀጠልን።

ወደ እዛ እየሄድን እያለ "ግን አባቴ አይፈቅድ ይሆናል" አለቺኝ። አባቷ ለምን ላይፈቅዱ እንደሚችሉ ሳስብ ግራ ገባኝ። በእኔ ቤት እኔ ተፈላጊ ወጣት ነኝ፤ ፈረንጅ አገር ተምሬ የመጣሁ፤ ባለ ጥሩ ደሞዝ ... ነኝ። "ለመሆኑ የማይስማሙት

ለምን እንደ ሆነ ታውቂያለሽን?" አልኳት፡፡ "አማራ ስለ ሆንህከ ብቻ" አለችኝ። በኢትዮጵያውያን መካከል እንደዚህ ያለ ስሜት መኖሩ ያኔ ለእኔ እንግዳ ነገር ነበር፤ በተለይ እኛ ሐረሮች እንዲህ ያለ ስሜት ፈጽሞ አልነበረንም፡፡ በሰማሁት ተገርሜ "እንግዲህ እናያለና!" ተባብለን አጎቷ ቤት አድርሺያት ሻሸመኔ ድረስ ሂጄ እንድጎበኛት እቅድ አውጥተን ተለያየን።

***

በማግሥቱ ወደ ሻሸመኔ ሄደች፤ ከዚያ በኋላ በየአስራ አምስቱ ቀን ጉዞ ወደ ሻሸመኔ ሆነ፡፡ የምመላለሰው በአንበሳ አውቶቡስ ለለ ሆነ መቀመጫ ለማግኘት በሌሊት ወደ አውቶቡስ ጣቢያ መሄድ ነበረብኝ፡፡ በጧት መድረሱ ስለማይሳካልኝ ዘግይቼ እደርሳለሁ፡፡ ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ የምጓዘው ሹፌሩ ጎን ሞተሩ ላይ ተቀምጬ ከሹፌሩ ጋር እያወራሁ ነበር። ሻሸመኔ እንደ ደረስሁ የጉዞዬን ድካም የሚያስረሳ የጾሮ ወጥ ይጠብቀኝ ነበር፡፡ ከምሳ በኋላ ግቢው ዉስጥ እየተንሸራሸርን እናወጋለን፡፡ እንዲህ ያለ ነገር ያልተለመደ በመሆኑ ሰው ሁሉ በአድናቆት ያየን ነበር፡፡ እሁድ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ አብረን እንዘምር ነበር፡፡ የምናዘወትራቸው መዝሙሮች ሁለት ነበሩ፤ አንዱ "የዘላለም ምርጫዬ ነህ" የሚለው ሲሆን ሌላው ከበየነ ጭምጫይበሉ ጋር የዘመርነው "ስራመድ ስጓዝ" የሚለው ነበር፡፡ የሁለቱም መዝሙሮች የመጀመሪያ ቁጥሮች እነሆ።

የዘላለም ምርጫዬ ነህ ወዳጄና ህይወቴ

በጉዞዬ ካንተ ጋራ ልራመድ መድሃኒቴ

ካንተ ጋር፡ ካንተ ጋር፤ ካንተ ጋር፡ ካንተ ጋር

በጉዞዬ ካንተ ጋራ ልራመድ መድሃኒቴ።

***

ስራመድ ስጓዝ በፀሐይ ብርሃን

በረግረግ ዉስጥ በተራራም ላይ





የሱስ በሎናል አልተዋችሁም

በማይወድቀው በጽኑ ተስፋው

የሰማይ ብርሃን የሰማይ ብርሃን

ነፍሴን ያጎርፋል በክብሩ ኃይል

ሃሌ ሉያ እደሰታለሁ እዘምራለሁ ለየሱሴ።

ብዙዎች አብረን ቆመን መዘመራችንን ያደንቁልን ይወዱትም ነበር። መተዋወቃችን ቀጠለ፤ አባትዋና እርሷ በጣም ይቀራረቡ ስለነበር አንድ ቀን ጠጋ ብላ እጮኛ ሊሆናት የሚችል ማግኘቷን ነገረቻቸው፡፡ ሲመልሱም "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል መልካም ነው" ማለታቸውን ነገረችኝ፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ እራሷን በጣም ስላመማት ወደ ልዕልት ፀሃይ ሆስፒታል መጥታ መታከም ነበረባት፡፡ የራስ ምታት ያመማት ለምን እንደሆነ አላወቅንም፤ ፍቅር ነው እያልሁ እቀልድባት ነበር፡፡ አንድ እለት ልጠይቃት ሆስፒታል ሄጄ ተኝታ እያለች እርሷ ላይ ያለችኝን ትንሽ ቅሬታ ገለጽኩላት፡፡ በዚያን ዘመን የጥሩ ሜኖናይቶች አቋም ስለነበርኝ ጌጣጌጧን አልወድም ነበር፡፡ ከዛም በፊት ስለጌጥ አቋሜን በመጠኑ ነግሬአታለሁ፤ ሆስፒታል ተኝታ ይህን ጉዳይ አነሳሁባት፤ "ከተገናኘን ጀምሮ በምን አሳዝኜህ አውቃለሁ?" አለችኝ፡፡ ደንገጥ ብዬ "አይ አሳዝነሺኝ አታውቂም፤ እኔስ?" አልኳት፡፡ "ስለዚህ ጉዳይ ከአሁን ቀደምም አንስተኸብኛል፤ የማያስደስትህ ከሆነ ያውልህ" በማለት በጣትዋ ያለች አንዲት የወርቅ ቀለበትና ጆሮዋ ላይ ያለውን ጉትቻዋን አውልቃ አልጋው ላይ ወረወረቺው፡፡ በአርምጃዋ ደንገጥ ብዬ "እንዲህ አድርጊ ለማለት አይደለም፤ ብቻ ወደፊት የምንቀጥል ከሆነ እንድታሰቢበት ያህል ነው" አልኳት።

ያን ለት ማታ ጠይቄአት ወደ ቤቴ ስመለስ ያለቺኝን ሳሰላስል እውነትም ከዚህ ከወርቅ ሌላ እስከዚያ ቀን ቅር የተሰኘሁበት ምንም ነገር አልነበረም፡፡ ይቺን ልጅ ማግባት አለብኝ በማለት ወሰንሁ፡፡ ከሆስፒታል ስትወጣ በደኖና ድሬዳዋ አገልግሎት ስለነበረብኝ ይገርአት ወደ እዚያ ሄድሁ፡፡ ከዛ ስንመለስ ሽማግሌ

ላከኹ፡፡ አባትዋ ቀድሞ እንቺ የመረጥሺው ይስማማኛል ቢልዋትም ለሽማግሌዎች የአሺታ መልስ ሳይሰጡ መሰሏቸው፡፡ እኛ መገናኘታችንን ቀጠልን፤ የአባቷ ዝምታ ይበልጥ አቀራረበን፡፡ በዚያን ወቅት የእናትዋ ወንድም (የቅርብ አጎቷ) ከአስመራ መጥተው ነበር፡፡ ወደ አስመራ ሲመለሱ እንዳስተናግዳቸው ግደይ ወደ እኔ ልካቸው ስለ ነበር በማግስቱ ወደ አሥመራ ሲሄዱ እኔ ቤት አድረው ነበር። ምክራቸውን ሲለግሱኝ እንዲህ አሉኝ፡-

"ግራዝማች ልቡን አጠንክሯል፤ ከእናትዋ ጋር ተማክሬአለሁ፤ እኔ ግን የምመክርህ እንድታገባት ነው፤ ነገር ግን ወደ ባሪያ አገር እንዳትወስዳት!"

***

## ሠርግ

የወላጆችዋ እምቢታ የጋብቻ ቀናችንን አፋጠነው። አስገድደው ለሌላ ሰው ሊድሯት እያቀዱ እንደሆነም ጭምጭምታ መስማትዋን ነገረችኝ፡፡ ስለዚህ የሠርጋችንን ቀን ሚያዝያ 25 ቀን 1951 ዓ.ም በራስ ተሰማ ሰፈር በሚገኘው መሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ፡፡

በሠርጋችን ዕለት የሰበኩት ሚስተር ዌንገር ሲሆኑ፣ ሥነ ሥርዓት ያከናወነው ጋሼ ገብረ ሥላሴ ሐብታሙ ነበር። ከዚህ በፊት የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆኖ ያገባ በዚህ መልክ ጋብቻ የፈጸመ አልነበረም፡፡ ስለዚህም የጋብቻ ቃል ኪዳን ማስፈጸሚያ ስርአት ስላልነበረን ከሜኖናይት የስርአት መጽሐፍ ተርጉሜ ለጋሼ ገብረ ሥላሴ የሰጠሁት እኔው ነበርኩ።

ሠርጋችን በጣም ቀላልና ቀልጠፍ ያለች ነበረች፤ ከሥነ ሥርዕቱ በኋላ በኤስ. ኤይ.ኤም. እንግዶች ማረፊያ የለስላሳ መጠጥና የብስኩት ግብዣ ተደረገልን፡፡ ብስኩቶቹን ያዘጋጁት የሜኖናይት ሚስዮናውያን ነበሩ።

ከታዳሚዎቹ መካከል ወላጆቼ፣ አከስቴ ስበነ፣ በኩር ልጇ ጋሼ ይልማ ተሰማ ይገኙበታል፡፡ ከግደይ ዘመዶች ማንም አልተገኙም። እህቷ ንግሥቲ ያንስት ቢንያምን ወልዳ ናዝሬት ኃ.ማ.ማ.ሞ. ሆስፒታል ተኝታ ነበር፡፡





በመኖሪያ ቤታችን ያደረግነው ዝግጅትም እንዲሁ ቅልብጭ ያለች ነበረች፡፡ ለእርድ ያዘጋጀሁት አንድ በግ ብቻ ነበር፡፡ እናቴና አከስቴ ያንን አዘጋጅተው ከሚዜዎቼና ከቤተ ሰቤ ጋር እራት አደረግናት፡፡ ከሚዜዎቼ መካከል ንጉሤ አያለና ጸጋ ወልደ ማርያም፣ በየነ ጭጫይበሉ፣ አበባ ወልደ ሩፋኤል እዚያው ትንሿ ቤቴ ሲያድሩ ሌሎች ጓደኞቼ ወደ ቤታቸው ሄዱ። በማግስቱ እኔና ግደይ ለጫጉላ ሽርሽር ወደ ወሊሶ ተጓዝን፡፡ ለግደይ ወላጆች ደብዳቤ ጽፌን አሸብር ሻሽመኔ ድረስ ሄዶ እንዲያደርስ አደረግን።



## ህልምም - እውነትም

ወሊሶ ለሜጉላ ሽርሽር በሄድንበት የመጀመሪያ ሌሊት አዳራችን ላይ ህልም አለምሁ:: በህልሜ በዋሻ ውስጥ (ተራራ ተሸንቁሮ ውስጥ ለውስጥ በተዘረጋ መንገድ) የምሄድ ይመስለኛል:: አሜሪካ በነበርኩበት ጊዜ በፔንሲልቫኒያ ተርንፓይክ ላይ አምስት ማይልስ ርዝመት ባለው ዋሻ ውስጥ ተጉዤ አውቃለሁ። አጭር ነች እንጂ ደብረ ሲና ከተማ ሊደረስ ሲል እንዲህ አይነት ዋሻ መንገድ አለ:: በእንደዚያ ያለ ረጂም ዋሻ ዉስጥ የምሄድ ይመስለኛል:: በዋሻው ዳር ያለው ገደል ዉስጥ ገባሁ፤ ለመውጣት ብሞክር አልቻልኩም፤ ለመውጣት የሚረዳኝ ሰው ፍለጋ መጮህ ያስፈልገኛል አልኩና ጮህኩ:፡ አጠገቤ ባለው አልጋ ላይ ተኝታ የነበረቺው ግደይ ምን መጣ ብላ በታላቅ ድንጋጤ ተነሳች:: ከዚያ በኋላ የነበረውን ለማስረዳት አይቻለኝም። ብቻ:- ምኑን ነው የአገባሁት? ላትል አልቀረችም።

***

ከወሊሶ ከተመለስን በኋላ፥ አባባ ዘሚካኤልን በደንብ የሚያውቁ ኤርትራውያን ሽማግሌዎች ፈልገን ላክን:: በብዙ ችግር እርቅ ወርዶ መልሰም ተጠራን። በመልሱ ላይ አባቴና እናቴም እንዲገኙና ከግደይ ቤተሰቦች ጋር እንዲተዋወቁ አደረግኹ።

ነገሮች ከሰከኑ በኋላ ዘወር ብለን ትዳር አጀማመራችንን ስንመለከት፣ ያለ ግደይ ወላጆች ፈቃድ መጋባታችን ልክ አልነበረም:: ቢያንስ ከመጋባታችን በፊት እሺታቸውን ለማግኘት መጣር ነበረብን፤ በጣም ተቻኩለን ነበር:: በመቸኮላችን የተነሣ ስለ ትዳር በጋራ ምንም አይነት ትምህርትና ሥልጠና እንኳን አልወሰድንም ነበር:: ለምሣሌ:- ፍቅር፣ ተግባቦት (ግንኙነት)፣ ግጭት የሃሳብ መለያየትና ስለ መፍትሔው፣ እንዲሁም ስለ ገንዘብ አጠቃቀምና፤ የልጆች አስተዳደግ፣ በተጨማሪም በትዳር ውስጥ ስለሚከሰቱ ሦስተኛ ወገኖች ማለትም ከዘመድ አዝማድና ወዳጆች ጋር ሊኖረን ስለሚገባው ቅርበትና ርቀት ልክ . . . ወዘተ ጉዳዮች መማር እንደ ነበረብን የተረዳነው ዘግይተን ነበር።

እኔና ግደይ በወጣትነታችን ያጎደልናቸውን እነኚህን ነገሮች የምገልጸው መጽሐፉን ለሚያነቡ ወጣት ወገኖቼ ትምህርት ይሆን ዘንድ ነው። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ጸጋውን ስላበዛልን የዚህ መጽሐፍ ረቂቅ ሲዘጋጅ እንኳን በትዳር ከተጣመርን 58 ዓመት ሞላን:: ቆይታችንን በቀላሉ ብናስላው እንኳን የአንድ ሰው ዕድሜ ነው እኮ! ከእንግዲህ በኋላ ምን ያህል የአብሮነት ዕድሜ እንደሚጨመርልን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እነዚህን ሁሉ አመቶች በትዳር ስንጓዝ በየመንገዱ ብዙ ጊዜ ተጣልተናል፤ እንፋታም እስከ መባባል የደረስንበት ጊዜ ነበር:: እንዲህም ሆኖ ተቻችለን አብረን እንድንዘልቅ የረዳንና ጸጋውን ያበዛልን እግዚአብሔር ይመስገን::

እንግዲህ መጀመሪያ እኔና ግደይ ወሊሶ አብረን ያደርን ዕለት ያየሁት ህልም ትርጉሜ ይህን የሚያመለክት ይመስለኛል።

***

## ድክ-ድክ - ወደ አገልግሎት መሪነት

ተግባረዕድ ሳስተምር መንፈሳዊ አገልግሎቴ ያተኮረው በመርሐ እውራን ት/ቤት በሚደረገው ሳምንታዊ የእሁድ ጠዋት ፕሮግራም ላይ ነበር። በተጨማሪም በኤስ አይ ኤም የወጣቶች ማዕከል ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ በሚካሄደው «በወጣት ለክርስቶስ» ፕሮግራምም አጫጭር መዝሙሮች (አዝማቾች) እዘምርም ነበርሁ።

በየነ አለማየ እርሻ ኮሌጅ፣ ሌሎች ጓደኞቼ ማለት ኃይሌ ወልደ ሚካኤልና ንጉሴ አየለ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ትምህርታቸው ላይ አተኮሩ። የእሁዱ ፕሮግራም መሪነት በኔ ላይ ወደቀ:: እነ ንጉሴ እኔን 'ፓስተራችን' እያሉ ይቀልዱብኝ ነበር።

በአዲስ አበባ የማምለኪያ ቤት መፈለግ የጀመርነው ያኔ ነበር። አብረን ከምናመልከው ውስጥ አብዛኛዎቹ የመርሃ ዕዉራን ተማሪዎችና የዩኒቨርሲቲ

ተማሪዎች ሲሆኑ ከውጭ የምንመጣው ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰፈር የሚኖሩ ባልና ሚስት እና እኛ ነበርን። ጸሎት ቤት የሚሠራበት ቦታ የት ይፈለግ ሲባል ወደ እኛው ሰፈር ቢሆን ይሻላል ተባለና በደላላ አማካይነት በተግባረዕድ ት/ቤትና ልደታ አካባቢ የሚሸጥ ቦታ ማፈላለግ ጀመርሁ። አሁን የጌኛ ቃለ ሕይወት የተሠራበትን ቦታ አግኝቼ ከሦስት ሴት ባለ ንብረቶች ላይ፣ በእኔ፣ ኃይሌና ደስታ አለሙ ስም ተገዛ። ከጊዜ በኋላ ቦታው ለቃለ ሕይወት በሽያጭ ተላለፈ፤ በምትኩ ወደ ቦሌ መንገድ ላይ ቦታ ተገዝቶ ደርግ እስኪዘጋው ድረስ የተገለገልንበት የቦሌ መሠረተ ክርስቶስ ጸሎት ቤት ተሠራ::

በዚያን ዘመን በሚስዮን ስም መሬት ሊገዛ አይቻልም፤ ቤተ ክርስቲያንም አትታወቅም ነበር። በሰማችን የተገዛው ቦታ የኛ እንዳልሆነ አቶ ሕይወት ጎዳሩ የሚባሉ የህግ አዋቂ (ጠበቃ) አሰፈረሙንና የፈርምንበት ወረቀት በሚስዮኑ ቢሮ ተቀመጠ። በነገራችን ላይ በናዝሬት የመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ የነበረበት ቦታም የተገዛው በዚሁ ዘዴ ነበር (በገመዳ ባሩዳ፣ ንጉሤ አየለና ገብረ ሥላሴ ሐብታሙ ስም የተገዛ)።

## ቢሊ ግርሃም በአዲስ አበባ

በ1951 ዓ.ም. ከተከሰቱ ታላቅ መንፈሳዊ ነገሮች አንዱ የቢሊ ግርሃም ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በኳስ ሜዳ ጀማ የወንጌል ስብከት መደረግ ነበር። ፕሮግራሙ የተቀነባበረው በዚያን ጊዜ በነበሩ የወንጌላውያን ሚሲዮን ድርጅቶችና አጥቢያ ቤተ ክርስቶያናት አማካኝነት ነበር::

በመርሃ አውራን የሚደረገው የሜኖናይቶች አጥቢያ እንደሆነ ተቆጥሮ ከዛ የተወከልኩት እኔ ነበርሁ። የአዘጋጅ ኮሚቴው ሊቀ መንበር የመካነ እየሱስ አቶ አማኑኤል ገብረሥላሴ (አሁን ዶር.) ነበሩ። በእሳቸው አማካይነት እኒህ በመላው አለም የታወቁ የወንጌል ሰባኪ ሌሎች ብዙ የአፍሪቃን ኮተሞች





ከጎበኙ በኋላ አዲስ አበባ የሚመጡ መሆናቸው ስግርማዊ ጃንሆይ ተነገረ:: ጃንሆይ ስብሰባው በኳስ ሜዳ እንዲደረግ ከመፍቀዳቸውም በላይ ተማሪዎች በስብሰባው ላይ መገኘት እንዲችሉ በነዚያ ሶስት ቀናት ከሰአት በኋላ ትምህርት እንዳይኖር አዘዙ። ኳስ ሜዳዋ በተማሪዎች ተሞላች።

ዝግጅቱ ብዙ ጊዜ ፈጅቶብናል። ጌታን ለመቀበል እጃቸውን የሚያነሱ፣ ከዚያም በኋላ ወደ ፊት የሚመጡትን እንዴት ማስተናገድ እንደሚገባ፣ የምክክርና የክትትል ስርአት ስልጠና ቀደም ብሎ ተሰጠን:: ለዚህ ተብሎ ካርዶችና ለሚወስኑት የሚሰጡ ጽሑፎች መዘጋጀት ነበረባቸው:: ጌታን ለሚቀበሉ የሚሰጣቸውን አንዲት አጭር ጽሑፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተርጎምኩት እኔ ነበርኩ። ይቺም ዶክተር ቢሊ ግርሃም የሚሰጡአት አራት ነጥብ ያዘለች ምክር ነበረች።

«መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ አንብብ፣

መጽሐፍ ቅዱስህን ካነበብህ በኋላ በየቀኑ ጸልይ፣

ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ይኑርህ፣

ጌታ ያደረገልህን ለሌሎች መስክር»።

ስብከታቸው በአቶ አማኑኤል ገብረ ሥላሴ አስተርጓሚነት ተሰጠ::

ስብከት ሲጀምሩ ሌሎች የአፍሪቃ አገሮችን ጎብኝተው እንደ መጡ ከገለጹ

በኋላ፡- “ወንጌል ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ወደ እኔ አገር አሜሪካና ሌሎች አገሮች ከመሄዱ በፊት ነው፤ ወደ ቀሩት የአፍሪቃ አገሮች ሚስዮናውያን መላክ የነበረባችሁ እናንተ ነበራችሁ፤ ለምን አልላካችሁም?” በሚል ጥያቄ ስብከታቸውን ጀመሩ።

ትንሽ እንደ ሰበኩ ዝናብ መዝነብ ጀመረ:: ለእርሳቸውና ለአቶ አማኑኤል የዝናብ ልብስ ተሰጠና መስበክ ቀጠሉ:: ህዝቡም በዝናብም ቢሆን መስማት ቀጠለ። የስብከቱ ቀን እንደታቀደው ያልሄደው የምክክሩና የክትትሉ ነገር ነበር::

ዶክተር ግርሃም በስብከታቸው መጨረሻ ጌታን የምትቀበሉ አጃችሁን አንሱ ሲሉ ሁሉም እጁን አነሳ። ይህ ነገር አልገባችሁም ብለው አስረዱ፤ ታላቅ ዋጋ እንደሚያስከፍል ጨምረው ተናግረው እንደ ገና አጃችሁን አውጡ አሉ፤ የወጣው እጅ ቁጥር ያው ነበር።

እዚያው ባሉበት ከላይ የተጠቀሱት ምክሮች ተሰጥተዋቸው ሄዱ። በራሪ ጽሑፎች ግን በበቂ ሁኔታ አልታደሉም ነበር። ምክንያቱም ለዚያ ሁሉ ህዝብ የሚበቃ አላሳትምንም ነበርና።

ወደዚያ ስብሰባ የሄዱት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ቢሆኑም በየከተማው በየቦታው ስለ ወንጌል ይወራ ነበር፡፡ እኔ በማስተምርበት በተግባረ ዕድ ት/ቤትና በዚያው ግቢ ዉስጥ ባለው መሐንዲስ ኮሌጅ የሚወራው ይሄው ነበር፡፡ እኔና ማሞ ገ/መስቀልን ሌሎች ጓደኞቻችን "ይህ ሁሉ ምድነው?" በማለት ጠየቁን፡፡ ከዚህም የተነሣ ከቢሊ ግርሃም ረዳቶች አንዱን ስመሐንዲስ ኮሌጅ ተማሪዎችና ለአስተማሪዎች ንግግር እንዲያደርግ ጠርተን ነበር፡፡ ያ ሰው መጥቶ ስለ እምነት ትምህርት ሰጥቶ ሄደ። ምን ያህል እንደ ገባቸው ባናውቅም እንዲያስቡ እንዳደረጋቸው እናምናለን። ስለ ማመን የሰጠውን ምሳሌ አሁንም ድረስ አስታውሳለሁ። እንዲህ ነበር ያለው:-

"በአንድ አዳራሽ ሁለት ምሰሶዎች ተተክለዋል፤ ከአንዱ ምሰሶ ወደ አንዱ ገመድ ተወጥሮአል፤ አንድ የአክሮባት ስፖርተኛ በዚች ገመድ ላይ ከአንድ ጥግ ወደ ሌላው ለመሻገር መራመድ ጀመረ፡፡ ህዝቡ ከአሁን አሁን ተፈጥፍጦ ሊሞት ነው ብሎ በስጋትና ፍርሃት ይጠባበቅ ጀመር፡፡ ስፖርተኛው ጉዞውን በዚያቺው ገመድ ላይ ቀጠለና ተሻግሮ ጨረሰ፡፡ ሰው አጨበጨበ፡፡ በመቀጠል ጋሪ እየገፋ ተሻገረ፤ ተጨበጨበለት፤ ቀጥሎም በጀንያ አህል ሞልቶ ተሸክሞ አሻገረና ዱብ አደረገ ተጨበጨበለት፡፡ ተመልካቾቹን እንዲህ በማለት ጠየቀ "ስንቶቻችሁ አንድ ሰው ትከሻዬ ላይ አድርጌ ላሻግር እንደምችል ታምናላችሁ?" አላቸው። ብዙ ሰዎች "ትችላለህ" ብለው አጃቸውን አነሱ፡፡ አጃቸውን ካነሱት ውስጥ ከፊት ያለውን አንዱን "ና እስቲ ይገፍህ ልሻገር" ሲለው እምቢ አለ፡፡ ሲላ ጠየቀ "አልፈልግም" አለው፡፡ ተሸክሞ ለማሻገር ማንንም ሊያገኝ አልቻለም። "በክርስቶስ ማመን ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን ስለኔ ኃጢአት ሞተሃል፤ በዚች አለም ዉስጥ ደግፈህ ዘለአለማዊ ቤቴ እስክገባ ድረስ ተሸክመህ ልታሻግረኝ ትችላለህ ብሎ ህይወትን ለእርሱ መስጠት ነው" አለ።



ትውስታዬ

***

ቢሊ ግርሃም ከሄዱ በኋላ ማሞ ገብረ መስቀል እና እኔ "ኢየሱስ ክርስቶስን ከሚስዮን ግቢ ማውጣት አለብን" የሚል ሃሳብ መጣብን። በዚያን ዘመን ወንጌል የሚሰበከው በሚስዮን ግቢ ብቻ ነበር። በአሁኑ ሆቴል ዲአፍሪክ ፊትለፊት እንዲት ትንሽ ቤት ተከራየንና ቅዳሜ ከሰአት በኋላ በዚያች መስበክ ጀመርን፡፡ እንደ ፓል ጊንግሪክና አልበርት ብራንት ሚሲዮናውያንም እዚያ መጥተው እንዲሰብኩ እናደርግ ነበር፡፡ ያኔ ማሞ ተማሪ ስለ ነበር ለቤት ኪራይ የምከፍለው እኔ ብቻ ነበርኹ፡፡ ይህ በመሆኑ ለሁለተኛ ጊዜ በስኮላርሺፕ ወደ አሜሪካ ስሄድ ፕሮግራሙ ለጥቂት ወራት ከተካሄደ በኋላ ተቋረጠ፡፡